# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 045 ጥቅምት 15 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

DERBA CEMENT



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# ብልጽግናችን የሚሳለጠው ውስጣዊ አቅማችንን አሟጠን ስንጠቀም መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሳሰቡ



ፎቶ - ዳኜ አበራ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ወደ ብልጽግና የምናደርገው ጉዞ የተሳለጠ የሚሆነው በውስጣዊ አቅማችን ላይ ከተመሠረተ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)አሳሰቡ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትናንት በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት፤ ውስጣዊ አቅማችን ማለት የሕዝባችን አቅም፣ የሀገራችን ተፈጥሯዊና ታሪካዊ ሀብት እንዲሁም የአዲሱ ትውልድ የፈጠራ ክህሎት ናቸው ብለዋል፡፡

በአስቸጋሪ ፈተናዎች ውስጥ እያለፍን እንኳን ችግር ተቋቋሚ ኢኮኖሚ ሊኖረን ችሏል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ የዚህ ዋነኛ ምክንያቱ በመጠኑም ቢሆን ያሉንን ውስጣዊ አቅሞች አሟጠን ለመጠቀም መነሣታችን ነው ብለዋል።

ከየትኛውም ወገን የሚሰጠን ድጋፍ በውስጣዊ አቅማችን ላይ ተጨማሪ እንጂ ዋና የዕድገት ምንጭ ሊሆን

ብልጽግናችን የሚሳለጠው... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ደመቀ መኮንን

# በወሳኝ ስታትስቲክስ ሂደቶች ውስጥ ጉልህ እመርታ ተመዝግቧል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት በወሳኝ ስታትስቲክስ ሂደቶች ውስጥ ጉልህ እመርታ አስመዝግቧል ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን አስታወቁ። የአፍሪካ የሲቪል ምዝገባና ቫይታል ስታትስቲክስ ባለሙያዎች ጉባኤ በአዲስ አበባ እየተካሄደ ነው፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ትላንት በተጀመረው የአፍሪካ የሲቪል ምዝገባና ቫይታል ስታትስቲክስ ባለሙያዎች ጉባኤ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ በአፍሪካ የስታትስቲክስ ሥርዓቶችን በማሻሻልና በማዘመን ላይ ትልልቅ ስኬቶች መመዝገባቸውን ገልጸዋል።የኢትዮጵያ መንግሥትም በወሳኝ ስታትስቲክስ ሂደቶች ውስጥ ጉልህ እመርታ እያሳየ ይገኛል ብለዋል፡፡

በአፍሪካ ከመረጃ አያያዝ ጋር ተያይዞ የሚያጋጥመውን ተግዳሮት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ ያመለከቱት አቶ ደመቀ፤ ፖሊሲዎችንና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን

በወሳኝ ስታትስቲክስ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# መከላከያ ሠራዊቱ በሁሉም ዘርፎች ጠንካራ አቅም ፈጥሯል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ዘመናዊነትን መላበስን ጨምሮ በሁሉም ዘርፎች ጠንካራ አቅም መፍጠሩን የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ዛሬ የሚከበረውን የመከላከያ ሠራዊት ቀን አስመልክቶ በትናንትናው ዕለት "የጥንካሬያችን ምንጭ ሕዝባችን ነው" በሚል መሪ መልዕክት የፎቶ ዐውደ ርዕይ እና የፓናል ውይይትን ያካተተ የመክፈቻ ፕሮግራም ተከናውኗል፡፡

በትናንትናው ዕለት በመርሐ ግብሮቹ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስትር አብርሐም በላይ (ዶክተር)፣ የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ዘመናዊነትን መላበስን ጨምሮ በሰው ኃይል፣ በዲስፕሊን፣ በአደረጃጀት እና በልዩ ልዩ ዐውዶች የተለየ አቅም ፈጥሯል ብለዋል።

አሁን በመከላከያ ሠራዊት የተፈጠረው አቅም ከዚህ በፊት የነበረ ዓይነት አቅም አይደለም ያሉት ሚኒስትሩ፣ ሠራዊቱ አሁን በብዙ ዘርፎች የተሻለ አቅም ላይ ደርሷል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ጠላቶች ሳንቆም ሊጥሉን ፈልገው ብዙ እንደሞከሩ በመጥቀስ፤ አሁን ቆመንና ፀንተን የምናስቀጥልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል።በየትኛውም ኃይል የማይደፈር ሠራዊት ነው እየተገነባ ያለው ሲሉ ገልፀዋል፡፡

ከሩቁ የሚፈራ ሠራዊት እየገነባን ነው ያሉት ዶክተር አብርሐም፤ ይህ ግንባታ እየቀጠለ የሚሄድ መሆኑንና ሳይዋጋ የሚያሸንፍ እና ሳይዋጋ ውጊያን የሚያስቀር ሠራዊት እየተገነባ እንደሆነ አክለው ተናግረዋል፡፡

ፈታናዎችን በአንድነት እና በጽናት የማለፍ የኢትዮጵያ ታሪክ አሁንም በዚህ ትውልድ እየተረጋገጠ ነው ያለው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ የሚያፈርሳትም፣ የሚደፍራትም አይኖርም ሲሉ በአጽንዖት ተናግረዋል፡፡



የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስትር አብርሐም በላይ (ዶክተር)፣

ኢትዮጵያን ለመድፈርም ሆነ ለጠላት ተላላኪ ሆነው የሚያገለግሉት አካላት ደጋግመው እንዲያስቡ የሚያደርግ ሠራዊት መገንባቱን ሚኒስትሩ ገልጸዋል፡፡


ኢትዮጵያ፡- የአባቶቹን ታሪክ የሚደግም፣ ይህችን ሀገር አፅንቶ የሚያስቀጥል፤ የግዛት አንድነቷን በማንም እንደማይሸራረፍ በመስዋዕትነት የሚያረጋግጥ ጀግና፣ ጠንካራ እና በዲስፕሊን የታነፀ ወታደር ያላት ሀገር ናት ሲሉም አስረድተዋል፡፡

በዚሁ ዕለት ከ1900 ዓ.ም ጀምሮ ያሉትን የኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስትሮች እና ጠቅላይ ኤታማዦሮች ፎቶ ዐውደ ርዕይ ተመርቆ ተከፍቷል።ይህንን አስመልክተው የመከላከያ ሚኒስትሩ፤ ለኢትዮጵያ የላቀ አስተዋጽኦ ላበረከቱ የአገር ባለውለታዎች ዕውቅና መስጠትና ታሪካቸውን ሰንዶ ለትውልድ ማስተላለፍ ወሳኝ መሆኑን ተናግረዋል።

መከላከያ ሠራዊቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





# ‹‹አሸባሪው ትሕነግ ለውጭ ኃይሎች ጥቅም ሲል የሀገሩን ክብር ያዋረደ ቡድን ነው››

- ኤፍሬም ማዴቦ
የፖለቲካ ተንታኝ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ትሕነግ በስልጣን ዘመኑ ለውጭ ኃይሎች ጥቅም ሲል የሀገሩን ክብር ያዋረደ ቡድን ነው ሲሉ የፖለቲካ ተንታኙ ኤፍሬም ማዴቦ ገለጹ፡፡

የፖለቲካ ተንታኝ ኤፍሬም ማዴቦ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሸባሪው የትሕነግ ቡድኑ ለ27 ዓመታት ለውጭ ኃይሎች ጥቅም የሀገሩን ክብር አሳልፎ የሰጠና ያዋረደ ቡድን ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈጸመው በደልም ታሪክ ይቅር የማይለው ነው።

የውጭ ኃይሎች አሸባሪውን ቡድን ስልጣን ካስያዙ በኋላ ከኢትዮጵያ መውሰድ የሚፈልጉትን ሁሉ በመውሰድ በሀገሪቷ ላይ ችግር የሚያመጣ ፖሊሲን እንዲጠቀም ሲያደርጉት ነበር። የለውጡ መንግሥት

‹‹አሸባሪው ትሕነግ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








ገጽ 4

## የሕግ ማስከበር ዘመቻን የሚዳስስ “የእሳት ቀለበት” የተሰኘ መጽሐፍ ዛሬ ይመረቃል

ገጽ 4

ዜና

# "ብርጋዴር ጄኔራል ታደሰ የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄዎች በትምህርት እና በትውልድ እንደሚፈታ እምነት ነበራቸው"

- ወይዘሮ ፀሐይ ታደሰ ብሩ
የብርጋዴር ጄኔራል ታደሰ ብሩ ፋውንዴሽን መሥራችና ልጅ

**በሀይሉ አበራ**



አዲስ አበባ፡- የብርጋዴር ጄኔራል ታደሰ ብሩ 100ኛ ዓመት የልደት በዓል እና "ከደናኔ እስከ ፊንፊኔ" የመጽሐፍ ምረቃ ሥነ ሥርዓት ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች በተገኙበት በአዲስ አበባ ተካሄዷል።

በመድረኩ ንግግር ያደረጉት የጄኔራል ታደሰ ብሩ ፋውንዴሽን መሥራችና ልጃቸው ወይዘሮ ፀሐይ ታደሰ ብሩ፣ የኦሮሞ ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና፣ ማኅበራዊ የትግል ችግሮች መፍትሔ አግኝተው የማየት ሕልምና የጋለ ስሜት ስለነበራቸው እስከሕይወት መስዋዕትነት ድረስ መሥራታቸውን ተናግረዋል።

ወይዘሮ ፀሐይ ታደሰ ብሩ አባታቸው እስከ 17 ዓመታቸው እስከ 12ኛ ክፍል ካስተማሯቸው በኋላም "ካሁን በኋላ አንቺን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ማስተማር አለብኝ" ብለዋቸው የፊደል ሠራዊት የማቋቋም ሥራ መጀመራቸውንና "የተማረ ዜጋ መብቱን ይጠይቃል" የሚል ሀሳብ እንደነበራቸው ተናግረዋል።

ለትምህርት ብሩህ አዕምሮ ያላቸው ቢሆንም ከጣሊያን ወረራ ጋር ተያይዞ በለጋ እድሜያቸው እናትና አባታቸውን ማጣታቸው ፈተና ሆኖባቸው እንደነበር ጠቅሰዋል። በኢትዮ-ጣሊያን ጦርነት አባታቸው መገደላቸው፣ እናታቸውም በኃዘን ብዛት በወራት ልዩነት ሲሞቱባቸው በኃዘኑ ወደ ኋላ ሳይመለሱ በወኔ ዓላማቸውን ማስቀጠል ችለዋል ብለዋል።

ብርጋዴር ጄኔራል ታደሰ ብሩ ከራሱ አልፎ አገርን ጀግና አድርጓል ያሉት ወይዘሮ ፀሐይ የ100ኛ ዓመት የልደት በዓል ሲከበር የዛሬው ትውልድ ከእሱ የሕይወት አርአያነት እንዲማር ለማስቻል፤ እንዲሁም የአባታቸውን ሕልም ለማስቀጠል የተቋቋመው የብርጋዴር ጄኔራል ታደሰ ብሩ ፋውንዴሽን አስፈላጊውን ድጋፍ አግኝቶ እንዲንቀሳቀስ ለማስቻል መሆኑን አስታውቀዋል።

ብርጋዴር ጄኔራሉ ያጣውን የትምህርት ዕድል ልጆቹ እና ሌሎች ኢትዮጵያውያን የኦሮሞ ልጆች እንዲማሩ ብዙ ጥረት ማድረጋቸውን አስታውሰዋል። የፊደል ሠራዊት ኃላፊ በመሆንም "መማር ያስከብራል ሀገርን ያኮራል" በማለት በሰፊው ስለትምህርት ትኩረት እንዲሰጥ የለፉ መሆናቸውን ተናግረዋል።

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ፣ ጄኔራል ታደሰ ብሩ የኦሮሞ ሕዝብ ትግል በትምህርት እና በትውልዱ እንዲጠበቅ በማሰብ ማኅበረሰቡ እንዲማር ትኩረት አድርጓል። ትምህርት የትውልድ ጉዳይ በመሆኑ በአንድ ዘመን እንደማያበቃ የዛሬም፣ የወደፊቱም ጉዳይ መሆኑ ለጄኔራል ታደሰ ግልጽ ነበር ብለዋል። ከዳለኔ እስከ ፊንፊኔ መጽሐፍ ደራሲ ወይዘሪት ዙፋን ኡርጋንም አመስግነዋል።

በአፋን ኦሮሞ እና በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀውን መጽሐፉን 10 ሺህ ኮፒ ለትምህርት ቤቶች ለማከፋፈል እንዲሁም የብርጋዴር ጄኔራል ታደሰ ብሩ ፋውንዴሽንን ለመደገፍም ቃል ገብተዋል።

በመድረኩ የተገኙት የቀድሞ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት አቶ አባዱላ ገመዳ በበኩላቸው፣ "ብ/ጄኔራል ታደሰ ብሩ ከተወለደ መቶኛ ዓመቱ ቢሆንም ዛሬ ዳግም የተወለዱበት ቀን ነው" ሲሉ ተናግረዋል።

መጽሐፉ ለሚቀጥሉት ብዙ መቶ ዓመታት የታሪክ ማጠቀሻ ሆኖ እንደሚያገለግልም ጠቅሰው መጽሐፉን በጽናት በመጻፍ ለደረሰችው ወይዘሪት ዙፋን ኡርጋ ምስጋና እና አድናቆት አቅርበዋል። ወጣቷ በብዙ ልፋት መጽሐፉን ለዚህ አብቅታለች ያሉት አቶ አባዱላ ገመዳ እንደ ዙፋን ያሉት ወጣቶች ሀገሪቷ የምትፈልጋቸው መሆኑን አመላክተዋል።

ለትውልድ የሚተላለፉ መሰል ተግባራትን በመሥራት በማኅበረሰቡ ሰፊ ድርሻ ያላቸው ሰዎችን ታሪክ አውጥቶ ማሳየት ያስፈልጋልም ብለዋል።



# የወልዲያ – አላማጣ የከፍተኛ ኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ጥገና ተጀመረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ በተካሄደው ጦርነት ጉዳት የደረሰበት የወልዲያ–አላማጣ የባለ 230 ኪሎ ቮልት የከፍተኛ ኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መሥመር ጥገና መጀመሩን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ።

የመስመሩ መጠገን ከዓመት በላይ ኃይል ተቋርጦባቸው የቆዩ የላሊበላና ሰቆጣ ከተሞች እንዲሁም ሌሎች የዋግኽምራ ዞን አካባቢዎች የመብራት ኃይል እንዲያገኙ ያስችላል ተብሏል።

ከወልዲያ ዶሮ ግብር ማከፋፈያ ጣቢያ እስከ አላማጣ ማከፋፈያ ጣቢያ ድረስ በተደረገ ፍተሻ 50 ቦታዎች ላይ የኮንዳክተር ጉዳትና መበጣጠስ መድረሱ ተገልጿል።

አላማጣ ማከፋፈያ ጣቢያ ቀደም ሲል ከባህርዳር፣ አሸንዳ እና ኮምቦልቻ ከተዘረጉ መስመሮች ኃይል ያገኝ የነበረ ሲሆን ከባህርዳር–አላማጣ የተዘረጋው የኃይል ማስተላለፊያ መሥመር እስከሚጠገን ከኮምቦልቻ – አላማጣ ያለውን ባለ 230 ኪሎ ቮልት መሥመር የመጠገን ሥራ ተጀምሯል።

ጥገናው ሲጠናቀቅ ከአላማጣ ማከፋፈያ ጣቢያ በ66 ኪሎ ቮልት ኃይል ሲያገኙ የነበሩት የላሊበላ፣ ሰቆጣና ማይጨው መስመሮች ዳግም የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲያገኙ ያስችላል መባሉን ኢዜአ ዘግቧል።

የመሠረተ ልማት ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለማስጀመር በጥናት ላይ የተመሠረተ ሥራ እየተሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ቀደም ብሎ መግለጹ ይታወሳል።

አሸባሪው ሕወሓት በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ላይ በፈፀመው ጥቃት የትግራይና የተወሰኑ የአማራ አካባቢዎች እስካሁን የኤሌክትሪክ ኃይል ማግኘት አልቻሉም።

# ከቀያቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች ከ73 ሺህ ዩሮ በላይ ድጋፍ ተሰበሰበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ ምክንያቶች በተለይም በትሕነግ የጥፋት ቡድን ከቀያቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች ድጋፍ እንዲውል በተዘጋጀው "የእናት አገር ጥሪ ገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን" ጣሊያን ከሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን 73 ሺህ 83 ዩሮ መሰብሰቡ ተገለጸ።

በሮም የኢፌዴሪ ኤምባሲ ከሮም የእርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ እና በጣሊያን ዲፈንድ ኢትዮጵያ አስተባባሪዎች ጋር በመሆን ከቀያቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች ድጋፍ እንዲውል ባዘጋጁት የእናት አገር ጥሪ ገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን በጣሊያን፣ማልታና ግሪክ እንዲሁም ሌሎች አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵውያን ተሳትፈውበታል።

በጣሊያን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ልዩ መልዕክተኛ እና ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ደሚቱ ሐምቢሳ የበይነ መረብ ቴሌቶኑ መክፈቻ ሥነ ሥርዓት ባደረጉት ንግግር እንዳሉት፤ ዲያስፖራው አገር ስትጣራ ሁሌም አለን በማለት ለሚያደርገው ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ምስጋና ይገባዋል፤ አሁን ሀገራችን ለሚደርስባት ጫና የዲያስፖራው ድጋፍ ወሳኝ ነው። አሁንም ሁሉም የበኩሉን ድጋፍ ሊያደርግ ይጠበቃል ብለዋል።

የእለቱ የክብር እንግዳ ታዋቂው አርቲስት ስለሺ ደምሴ /ጋሽ አበራ ሞላ/ በበኩሉ እንደገለጸው፤ ለሀገራችን ምንም ዓይነት የምንቆጥበው ጉልበትም ሆነ ገንዘብ መኖር የለበትም፤ በጋራ ከቆምን የማንሻገረው ችግር እንደማይኖር እና ትልቅነት አንድ ከመሆን ብቻ እንደሚገኝ ገልፀዋል። በዕለቱ አትሌት ፋንቱ ሚልኬሳን ጨምሮ ሌሎች ታዋቂ ግለሰቦችም በሥነ ሥርዓቱ ላይ ተገኝተዋል።



አምባሳደር ደሚቱ ሐምቢሳ

የበይነ መረብ ቴሌቶኑን ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በየአካባቢያቸው በጋራ እና በተናጠል ሆነው ጨረታዎችን በመሳተፍ እንዲሁም ቀጥታ ድጋፎችን በማድረግ ተሳትፈዋል።

በበይነመረብ ቶሌቶኑ 73ሺህ 83 ዩሮ ድጋፍ የተሰባሰበ ሲሆን በዝግጅቱ የተሳተፉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵውያን ሀገራቸው በዘርፈ ብዙ ጫናዎች እያለፈች እንደሆነ በውል እንደሚገነዘቡ በመግለፅ፤ ወደፊትም ሀገራቸው ለምትፈልገው ድጋፍ መልስ ለመስጠት ከወትሮው በተለየ መልኩ ዝግጁ መሆናቸውን ገልፀዋል።

ዝግጅቱን አምባሳደር ደሚቱ ሐምቢሳ ባደረጉት የመዝጊያ ንግግር ኢትዮጵያውያኑ እና ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ ላደረጉት ድጋፍ እና ለሀገራቸው ለሚያሳዩት ቀናኢነት ምስጋና አቅርበዋል።



አምባሳደር አየለ ሊሬ

# አፍሪካ በጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ ወንበር እንዲኖራት ኢትዮጵያ ድምጿን ማስተጋባቷን ትቀጥላለች

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- አፍሪካ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ ወንበር እንዲኖራት በሚል ኢትዮጵያ የምታሰማውን ድምጽ ማስተጋባቷን ትቀጥላለች ሲሉ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዓለም አቀፍ ድርጅት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል አምባሳደር አየለ ሊሬ ተናገሩ።

የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ሥራ ላይ የዋለበትን ዓመታዊ “የተመድ ቀን” ክብረ በዓል ትናንትና በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ግቢ ተከናውኗል።

በወቅቱ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዓለም አቀፍ ድርጅት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄነራል አምባሳደር አየለ ሊሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የተመድ ጸጥታው ምክር ቤት የአፍሪካን ድምጽ እንዲያከብር የሚደረገው ጥረት ይቀጥላል።

እንደ አምባሳደር አየለ ሊሬ ገለጻ፤ ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን በላይ ሕዝብ የያዘችው አፍሪካ እስካሁን ድረስ በጸጥታው ምክር ቤት በቋሚነት ድምጽ የምታሰማበት ዕድል አለመፈጠሩ ስህተት ነው።

አፍሪካ በተመድ የጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ ጽምጽ ማግኘት አለባት የሚለውን ሃሳብ ኢትዮጵያ ቀጣይነት ባለው መልኩ ታቀርባለች ሲሉ ተናግረዋል።

አፍሪካም ድምጿን በቋሚነት የምታቀርብበት ዕድል እንዲፈጠር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና የተለያዩ ከፍተኛ የኢትዮጵያ ባለስልጣናት በዓለም አቀፍ መድረክ ድምጻቸውን አሰምተዋል፤ ኢትዮጵያም ይህንን አቋም በቀጣይ ጊዜያትም ማንጸባረቋን ትቀጥላለች ብለዋል።

በተመድ የጸጥታው ምክር ቤት አሁን ያሉት አምስት ቋሚ አባል አገራት ናቸው፤ ሌሎች 10 አገራት ደግሞ በጊዜያዊነት የሚያገለግሉ ተለዋጭ አባላት ናቸው። አፍሪካ ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት ያላቸው ቋሚ አባላት ውስጥ ድምጽ የላትም። ይህ ደግሞ የቢሊዮኖችን ሃሳብ ቦታ ያልሰጠ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

አምባሳደር አየለ እንደገለጹት፤ ከተመድ አባል ሀገራት ውስጥ ከአንድ አራተኛው በላይ አባላት የአፍሪካ ሀገራት ናቸው። በመሆኑም የአፍሪካውያን ድምጽ በአግባቡ ሊደመጥ የሚችልበትን መንገድ የማመቻቸት ኃላፊነት የሁሉም አካላት ነው።

ኢትዮጵያም በየመድረኮቹ ይህን ሃሳብ የምታንጸባርቀው የአህጉሪቷ ሕዝብ በተመድ ተገቢውን ውክልና እንዲያገኝና ውሳኔዎቹም በተገቢው መንገድ እንዲተላለፉለት ነው ብለዋል።

አምባሳደር አየለ እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያም ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ጋር በመሆን አህጉራችን በተመድ የጸጥታው ምክር ቤት ቋም ወንበር እንዲኖራት በመሥራት ላይ ትገኛለች፤ ይህን ጥረቷንም አጠናክራ ትቀጥላለች።

ኢትዮጵያ ለተመድ መመሥረት ምክንያት የሆነው የሊግ ኦፍ ኔሽን ሲቋቋም ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ብቸኛዋ ሀገር ሆኖ አባል ነበረች።

ከሊግ ኦፍ ኔሽን መፍረስ በኋላ ተመድ ሲመሠረት ኢትዮጵያ ነፃ ከነበሩ ጥቂት የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ አንዷ ሆና ለአፍሪካውያን መብት ስትሟገት መቆየቷ የሚታወስ ነው።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቃቱን ተከትሎ መሰል ጦርነቶችን ለመከላከል የተመሠረተው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት 77ኛ ዓመቱን በማክበር ላይ ነው።

# በቴሌ ብር ከ101 ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት ተካሂዷል

## - የሳይንስ ሙዚየሙ የነፃ ጉብኝት ጊዜ ለአንድ ወር ተራዝሟል

**ዳግማዊ ግርማ**




አዲስ አበባ፡- በቴሌ ብር አገልግሎት ከ101 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት ማስተናገድ መቻሉን ኢትዮ ቴሌኮም አስታወቀ። በኢትዮ ቴሌኮም እና በንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር መካከል የአገልግሎት ክፍያዎችን በቴሌብር ለመፈጸም የሚያስችል ስምምነት በትላንትናው ዕለት ተደርጓል። የሳይንስ ሙዚየም ነጻ የጉብኝት ጊዜ ለአንድ ወር መራዘሙም ተጠቁሟል።

ኢትዮ ቴሌኮም ትላንት ስምምነቱን ሲፈርም የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ፍሬሕይወት ታምሩ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ኩባንያው በቴሌ ብር አገልግሎቱ ከ101 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት (Transaction Value) ማስተናገድ ችሏል።

ኩባንያው በቴሌብር አገልግሎት እስከ አሁን ድረስ 24 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ደንበኞችን፣ 101 ዋና ወኪሎችን (Master Agents) ፣ 87 ሺህ ወኪሎች 23 ሺህ ነጋዴዎች /Merchants/ ማፍራት የቻለ ሲሆን፣ ከ101 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት ማስተናገድ (Transaction Value) ችሏል ብለዋል።

በተጨማሪም ከ16 ባንኮች ጋር ትስስር (Integration) በማድረግ ከባንክ ወደ ቴሌብር ገንዘብ ማስተላለፍ የተቻለ ሲሆን፣ ከ13 ባንኮች ጋር ደግሞ ከቴሌብር ወደ ባንክ የገንዘብ ዝውውር እየተደረገ ይገኛል ሲሉም ጠቅሰዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም የዲጂታል ኢትዮጵያን ራዕይ እውን የማድረጉን ጉዞ መጠነ-ሰፊ ሥራዎችን በቁርጠኝነት በማከናወን እየገፋበት የሚገኝ እንደሆነ ያመለከቱት ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ፤ ከንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር የመግባቢያ ስምምነት በመፈራረም የመሥሪያ ቤቱ ባለጉዳዮች ከንግድ ምዝገባ፣ ከንግድ ፈቃድ እና ከንግድ ስያሜ ጋር ተያያዥነት ላላቸው የአገልግሎት ክፍያዎች ያለምንም ውጣ ውረድ በኦንላይን አገልግሎት እንዲያገኙ እንደሚያስችል ገልጸዋል።

ስምምነቱ ቀላል፣ ፈጣን፣ ምቹና አስተማማኝ የሆነውን የዘመኑን የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ቴሌብርን ተጠቅመው የአገልግሎት ክፍያቸውን እንዲፈጽሙ ያስችላቸዋልም ነው ያሉት።

በተለይም የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ባለጉዳዮች ለአዲስ ንግድ ምዝገባ፣ ማሻሻያ፣ ምትክ እና የውል ማቋረጥ አገልግሎት ክፍያዎችን እንዲሁም አዲስ የንግድ ፈቃድ ለማውጣት፣ ለማሳደስ፣ ምትክ ለመውሰድ፣ ውል ለማቋረጥ/ለመሰረዝ፣ ለአዲስ የንግድ ስም፣ የንግድ ስም ለማሻሻል፣ ለመቀየር እና ለመሰረዝ የአገልግሎት ክፍያዎችን በቀላሉ በቴሌብር የክፍያ አማራጭ እንዲያከናውኑ ያስችላቸዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ባለጉዳዮች አገልግሎቱን ለማግኘት ወደ www.etrade.gov.et በመግባት እና የሚፈልጉትን የአገልግሎት አይነት በመምረጥ እንዲሁም የአገልግሎት ቅጹን በቀጥታ (online) በመሙላት ለአገልግሎቱ ክፍያ ለመፈጸም የሚሰጣቸውን የመክፈያ ቁጥር በመጠቀም በቴሌብር መተግበሪያ ወይም በቴሌብር አጭር ቁጥር (*127#) የአገልግሎት ክፍያቸውን በቀላሉ መፈጸም ይችላሉ ብለዋል።

በሌላ በኩልም ከበርካታ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና ድርጅቶች ጋር ስምምነት በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የክፍያ ሥርዓታቸውን በማቀላጠፍ ለተቋማቱም ሆነ ደንበኞቻቸው እፎይታን አጎናጽፏልም ብለዋል።

በቀጣይ ጊዜያትም ኩባንያችን ከሌሎች መሰል ተቋማት ጋር በመተባበር የክፍያ ሥርዓታቸውን በቴሌብር የሚተገብሩበትን አሠራር በማመቻቸት ደንበኞቻቸው የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እና የቴሌብር ደንበኞች በአንድ ሥርዓት ሁሉንም ክፍያ ባሉበት ሆነው እንዲፈጽሙ ለማድረግ እና የዲጂታል ኢትዮጵያን ራዕይ ዕውን የማድረጉ ተግባር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል እናረጋግጣለን ብለዋል።

በተያያዘ ዜናም የሳይንስ ሙዚየም የነፃ ጉብኝት ጊዜ ለአንድ ወር መራዘሙንም ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ ገልጸዋል።

እንደ ወይዘሪት ፍሬሕይወት ገለፃ፤ የሳይንስ ሙዚየሙን ለመጎብኘት ባለው ሰፊ ፍላጎት ምክንያት የመጎብኛ ጊዜውን መጨመር አስፈልጓል። የሳይንስ ሙዚየሙ በ19 ቀናት ውስጥ 357 ሺህ በላይ ሰዎች የጎበኙት ሲሆን ባሳለፍነው ቅዳሜና እሁድ ብቻ ከ109 ሺህ በላይ ሰዎች እንደጎበኙት ተናግረዋል።

መዚየሙን ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉ ሰዎች እንዲጎበኙት ለማድረግ የሚያስችል ሥራ እየተከናወነ መሆኑንም አስረድተዋል።

# በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት 14 ቢሊዮን ብር የሚያወጣ አገልግሎት ተሰጥቷል

## - 18 ሚሊዮን ወጣቶች ተሳትፈዋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን በ2014 ዓ.ም የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት 14 ቢሊዮን ብር የሚያወጣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠቱን አስታወቀ። በበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ 18 ሚሊዮን ወጣቶች መሳተፋቸውም ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ሙሕዲን ናስር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ መጥቷል። በ2014 ዓ.ም በተከናወነው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎትም መንግሥትና ሕዝብ ሊያወጡ ይችሉት የነበረን 14 ቢሊዮን ብር ማዳን መቻሉን ጠቁመዋል።

ፌዴሬሽኑ ከሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በትብብር መሥራት መቻሉ ከፍተኛ ውጤት አስገኝቷል ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ በተለይም የወሰን ተሻጋሪ ወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በዚህ ዓመት ከተከናወኑ ተግባራት ትልቅ ውጤት የተገኘበት ነው ብለዋል።

የወሰን ተሻጋሪ ወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ወጣቶች የሌሎች አካባቢዎችን ባህልና ወግ እንዲረዱ በማድረግ ሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት መጠናከር ትልቅ ሚና ያለው በመሆኑ በቀጣነትም በተጠናከረ መልኩ



አቶ ሙሕዲን ናስር

እንደሚሠራበት አስገንዝበዋል።

እንደ አገር የገጠመንን ችግር ለመወጣት የወጣቶች ሚና የማይተካ ነው ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ ለመከላከያ ሠራዊትና ለሌሎችም ሰብዓዊ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች የእርዳታ ማሰባሰብ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል። በቀጣይነትም ወጣቶችን በማስተባበር የሚደረገው እገዛ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በ2014 ዓ.ም በጎ ፈቃድ አገልግሎት 18 ሚሊዮን የሚጠጉ ወጣቶች መሳተፋቸውን አስታውሰው፣ አረንጓዴ አሻራ፣ የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት፣ ደም ልገሳና ሰብዓዊ ድጋፎች፣ የአቅመ ደካሞችን በሥራ ማገዝና ቤት መጠገን፣ የጤና መከላከል፣ የአካባቢ ጥበቃና የአካባቢን ሰላም ማስጠበቅ ፌዴሬሽኑ በክረምት በጎ ፈቃድ ካከናወናቸው የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች መካከል የሚጠቀሱ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ በተመረጡ ዘርፎች በበጋም እንደሚቀጥል ያመለከቱት አቶ ሙሕዲን፤ የትራፊክ አገልግሎት፣ የአካባቢን ሰላምን ማስጠበቅ፣ ደም ልገሣና ሌሎችም ሰብዓዊ ሥራዎችና የተተከሉ ዛፎችን መንከባከብ በበጋ ወቅት ከሚሠሩ ሥራዎች ውስጥ መሆናቸውን ተናግረዋል።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንደ አገር ያሉብንን ክፍተቶች ለመሙላት ጉልህ ሚና እንዳለው የጠቀሱት አቶ ሙሕዲን፤ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ወቅት ጠብቆ የሚሰጥ ሳይሆን ባህል ሆኖ ሁሌም መቀጠል ያለበት ነው። በመሆኑም የአገር ተረካቢ የሆኑ ወጣቶች በየአካባቢያቸው ያሉ ክፍተቶችን በመለየት በበጎ ፈቃድ እንዲሳተፉና ለሁለንተናዊ አገራዊ ለውጥ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል።

ዜና

# የሕግ ማስከበር ዘመቻን የሚዳስስ "የእሳት ቀለበት" የተሰኘ መጽሐፍ ዛሬ ይመረቃል

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- የመጀመሪያውን ዙር የሕግ ማስከበር ዘመቻ የሚዳስስ "የእሳት ቀለበት" የተሰኘ መጽሐፍ ዛሬ ይመረቃል።

በመከላከያ ሚኒስቴር ጥናትና ምርምር ማዕከል የወታደራዊ ንድፈ ሃሳብ ጥናት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር እና የመጽሐፉ ዝግጅት ኮሚቴ ዋና አስተባባሪ ኮሎኔል ሙላት ደሳለኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የመከላከያ ሠራዊት ቀንን በማስመልከት "የእሳት ቀለበት" በሚል የተዘጋጀው መጽሐፍ በዛሬው ዕለት ይመረቃል።

መጽሐፉን ለማዘጋጀት አንድ ዓመት ከስድስት ወር የሚጠጋ ጊዜ መውሰዱን የገለጹት ኮሎኔሉ፤ መጽሐፉ በሦስት ምዕራፎች የተቀነበበ መሆኑን አንስተዋል።

"የእሳት ቀለበት" መጽሐፍ የድርጊቱን ተዋናዮች እስከ ታች ድረስ ወርዶ በመጠየቅ የተዘጋጀ እንጂ በልብ ወለድ መልኩ የተፃፈ እንዳልሆነ በመግለፅ፤ መረጃዎች የሚሰባሰቡበት መንገድ ትኩረት ተሰጥቶ በጦርነቱ የተሳተፉ ሁሉም የጦር ክፍሎች የመረጃው ምንጭ እንዲሆኑ ተደርጓል ብለዋል።

በዚህም መሠረት ከሚያዝያ 20/2013 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ትግራይ ክልል በመሄድ በወቅቱ የነበሩ አራት ዕዞችን ያማከለ 11 መኮንኖች በማሠማራት ከሁሉም የጦር ክፍሎች መረጃ ከተራ ወታደር እስከ ከፍተኛው አመራር ድረስ መሰብሰብ መቻሉን ኮሎኔል ሙላት ገልጸዋል።

በሂደቱም ጦርነቱን የመሩ ከጄኔራል እስከ ኮሎኔል ማዕረግ ደረጃ ያላቸው 44 አመራሮችን በተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ መሠራቱን እና በጥቅሉ 1 ሺህ 685 ሰው የተሳተፈበት ውይይት ተደርጎ መረጃ መሰብሰብ መቻሉን አክለው ተናግረዋል። ሌሎች ተጨማሪ የመረጃ ምንጮችም እንደ ግብዓት መወሰዳቸውን ጠቁመዋል።

"የእሳት ቀለበት" መጽሐፍ በመጀመሪያው ምዕራፍ በሕወሓት ማኒፌስቶ ዙሪያ ሰፊ መንደርደሪያ የያዘ፣ ዕኩይ ተግባሩ በድንገት የመጣ ሳይሆን ገና ከአፈጣጠሩ ጀምሮ በቀረጸው ማኒፌስቶ የተያዘ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ ሰፊ ትንታኔ እንዲይዝ ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

ምዕራፍ ሁለት ደግሞ ሕወሓት ከለውጡ በኋላ ምን ዓይነት እንቅፋት የሆኑ ሥራዎችን በኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ላይ ይሠራ እንደነበር፣ በተለይ በሕዝቦች መካከል ይፈጥር የነበረው የጸጥታና ደህንነት ችግርን እንዴት ያስፋፋ እንደነበር፣ ሰሜን ዕዝን ለምን መካድ እንዳስፈለገውና በክህደቱ ሳምንታት በሠራዊታችን ላይ የፈጸመው ግፍና በደል በዝርዝር የቀረበበት ሰፋ ባሉ ንዑስ ርዕሶች የተደራጀ ምዕራፍ ነው።

ምዕራፍ ሦስት ደግሞ የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ከአፈና እራሱን አላቆ የመልሶ ማጥቃት በመሰንዘር በ17 ቀናት ጦርነት ትግራይን እንዴት ከጁንታው መንጋጋ እንዳላቀቀና የትግራይን ሕዝብ ወደ ተለመደው ማኅበራዊ ኑሮ እንዲመለስ ማድረግ መቻሉን ያሳያል። በሂደቱም የጦር ክፍሎቻችን ያደረጉት ተጋድሎና ገድል በዝርዝር የሚያሳይበት ሆኖ፣ በስትራቴጂና ኦፕሬሽናል ደረጃ ከተደመሰሰ በኋላ ትግራይ በቆየባቸው ስድስት ወራት "የሕግ ማስከበር ዘመቻውን" ብቻ የያዘ ታሪክ መሆኑን ያሣያል።

የመጽሐፉ ዝግጅት አስተባባሪ ኮሎኔል ሙላት፣ "የእሳት ቀለበት" መጽሐፍ ድርሰት ሳይሆን እውነተኛ የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ታሪክ የሆነና በውስጥ የሚጠቀሱ ማንኛውም ሥሞችና ቦታዎች የገድሉ ባለቤት ሠራዊታችን መሆኑን ማስገንዘብ እፈልጋለሁ ሲሉ ገልጸዋል።

# በትግራይ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለማስጀመር እየተሠራ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- መንግሥት በትግራይ ክልል ማኅበራዊ አገልግሎቶች የሚጀምሩበትንና ከየአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር በመነጋገር ሕዝባዊ አስተዳደር የሚቋቋምበትን መንገድ እያመቻቸ መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገለጸ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የወቅታዊ ሁኔታ መረጃ በሚል ትናንት በሰጠው መግለጫ እንደገለጸው፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሰብዓዊ የርዳታ ተቋማት ጋር በመቀናጀት በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች ሰብዓዊ ርዳታ እንዲደርስ እየሠራ ይገኛል።

የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት በእነዚህ አካባቢዎች አገልግሎት ለመጀመር የሚያስችል ዝግጅት እንዲያፋጥኑ እያደረገ ነው ያለው መግለጫው፤ ከየአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር በመነጋገር ሕዝባዊ አስተዳደር የሚቋቋምበትንና ማኅበራዊ አገልግሎቶች የሚጀምሩበትን መንገድ እያመቻቸ ይገኛል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ቁልፍ የሚባሉ የትግራይ ከተሞችን መቆጣጠሩን ቀጥሏል ያለው መግለጫው፤ ይህንን ሲያደርግም የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በከተሞች ውጊያ ሳይደረግ የሕወሓትን ወታደራዊ አቅም ለማሽመድመድ የሚያስችል ስልት ተጠቅሟል ብሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአፍሪካ ኅብረት በኩል በደቡብ አፍሪካ በሚደረገው የሰላም ንግግር መንግሥት የሚሳተፍ

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

መሆኑን መግለጫው አመልክቶ፤ አጋጣሚውንም የሰላም ንግግሩን ግጭቱን በሰላም ለመፍታት የሚቻልበት ዕድል አድርጎ ይመለከተዋል ብሏል። በመከላከያ ኃይላችን መሥዋዕትነት እየተስተካከለ የመጣውን ሁኔታ የበለጠ ለማጠናከር ምቹ አጋጣሚ የሚፈጥር አድርጎ ይወስደዋል ሲልም ጠቁሟል።

በሰላም ንግግሩ ላይ የሚሳተፈው የኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን ትናንት ጠዋት ወደ ደቡብ አፍሪካ ማምራቱንም የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መግለጫ አመልክቷል።

# ‹‹አሸባሪው ትሕነግ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከመጣ በኋላ ግን የውጭ ኃይሎች ጥቅም በመነሳቱ በኢትዮጵያ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳይ ላይ ጫና እንዲፈጠር አድርጓል።

በአሸባሪው ትሕነግ ሀገራዊ ክህደት ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ በኑሮ ውድነት፣ በብሔር ክፍፍልና መሰል ጉዳዮች ዋጋ እንዲከፍል ሆኗል። ባለፉት አራት ዓመታት ሀገሪቷ በአስቸጋሪና መጥፎ ሁኔታዎች ውስጥ እንድትጓዝም አድርጓታል። ይህም በውጭ ኃይሎች ተጽዕኖና በአሸባሪው ትሕነግ የተፈጠረ በመሆኑ ሊቆም ይገባል ብለዋል።፡

የኢትዮጵያ መንግሥት አሸባሪው የትሕነግ ቡድን ለ27 ዓመታት የሠራውን በደል ረስቶ ለሀገር ሰላም ሲል የሰላም አማራጭን አቅርቧል። ነገር ግን አሸባሪ ቡድኑ በውጭ ኃይሎች እየተመራ የኢትዮጵያን ሕዝብ ተዋግቼ አሸንፋለሁ የሚል እሳቤን አንግቧል። በመሆኑም የሚዋጋለት ዓላማን የማያውቅና የትግራይን ሕዝብ ለውጭ ኃይሎች ጥቅም ሲል ችግር ላይ እንዲወድቅ እያደረገ ያለ አሳፋሪ ቡድን ነው ብለዋል።

አሸባሪ ቡድኑ መንግሥት በተደጋጋሚ የሰጠውን የሰላም እድል አሻፈረኝ ብሏል።

ሁል ጊዜ ከጦርነት ይልቅ ነገሮችን በውይይት መፍታት የተሻለ ነው። አሸባሪው ትሕነግ ግን በውይይት የሚያምን ባለመሆኑ ኢትዮጵያ አሁን እያጋጠማት ላለው ችግር ተጠያቂ መሆኑን ሁሉም ሊገነዘብ ይገባል ብለዋል።

አሸባሪ ቡድኑ የድርድር እምነትና ባህል የሌለው ነው። ቡድኑ ድርድር ውስጥ ለመግባት ከፈለገም ሙሉ ለሙሉ ድርድሩ እሱ በሚፈልገው መንገድ መሆን አለበት። ይህ የሚያሳየው ደግሞ አሸባሪ ቡድኑ ለድርድርም ለጦርነትም የማይመች መሆኑን ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ያለው ችግር በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ከሆነ ሊታይ በሚችል መልኩ አሸባሪው ትሕነግ ትጥቁን መፍታት አለበት ያሉት የፖለቲካ ተንታኙ አቶ ኤፍሬም ማዴቦ፤ መንግሥት ሆኖ ሲመራ በነበረበት ጊዜና አሸባሪ በሆነበት ጊዜያት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በደል የፈጸሙ ሰዎችን በፍቃደኝነት ሕግ ፊት እንዲቀርቡ ማድረግ ይገባልም ብለዋል።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እየተቀያየረ ነው። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የውስጥና የውጪ ኃይሎች የሚፈጥሩት ተጽዕኖ ሀገሪቷ የምትሄድበትን አቅጣጫ በየጊዜው ሲቀያይር ተስተውሏል። አሁን ያለው መንግሥት ግን በዚህ ረገድ የተሻለ እንደሆነም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሀገርን ክብርና ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ባለፉት አራት ዓመታት በተሻለ አቋምና ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በሰሜኑ ጦርነት በተደረጉ እንቅስቃሴዎች ማየት ይቻላል ያሉት አቶ ኤፍሬም፤ የሠራዊቱ አቋም ኢትዮጵያ ከገባችበት መከራና ስቃይ ማውጣት እንደሚችል እተማመናለሁም ብለዋል።

# ብልጽግናችን የሚሳለጠው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አይችልም ሲሉም ገልጸዋል።

ውስጣዊ አቅማችንን ተጠቅመን ወደ ብልጽግና የምናደርገው ጉዞ ከዕንቅፋቶች የጸዳ አይደለም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ የኢኮኖሚ አሻጥር፣ ሌብነትና ምርት ስወራ ዋነኞቹ ፈተናዎቻችን ሆነዋል ሲሉም ጠቁመዋል።

ወደ ውጭ መላክ የሚገባውን ምርት መደበቅ፣ ሕገ ወጥ የውጭ ምንዛሪ ዝውውርና መሬትን በአሻጥር መውረር በቆራጥነት ፈጣን ርምጃ ልንወስድባቸው የሚገቡ የብልጽግና ዕንቅፋቶች መሆናውንም ገልጸዋል።

በቀጣይ ፈተናዎችን የሚሻገር ኢኮኖሚ ለመገንባት እንድንችል ሁለት መልክ ያሉት ትግል ያስፈልገናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ እነዚህም ማጥፋት እና ማልማት ናቸው ብለዋል።

የኢኮኖሚ አሻጥሮችን፣ ሌብነትንና ምርት ስወራን ለማጥፋት የሁላችንንም ወሳኝ ትግል ይፈልጋል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ገቢን የመጨመርና ወጪን በከፍተኛ ሁኔታ የመቀነስ የልማት ትግል ይጠበቅብናል ሲሉም አክለዋል።

እነዚህ ሁለቱ የትግል መስኮች በራሳችን ፖሊሲና በራሳችን አቅም ማደግ እንድንችል ያስችሉናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ምክንያቱም የዕድገታችን ቁልፍ በእጃችን ነውና ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# በወሳኝ ስታትስቲክስ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ተደራሽ ለማድረግ የስታትስቲክስ መረጃ ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል።

የስታትስቲክስ ሥርዓቶችን በማሻሻልና በማዘመን የአፍሪካ አባል ሀገራት መሥራት እንዳለባቸው የተናገሩት አቶ ደመቀ፤ የአፍሪካ መንግሥታት የአህጉራዊ መረጃ አካባቢን በብቃት ማዘመንና መለወጥ እንዲሁም በቂ በጀት መድበው የስታትስቲክስ ሥርዓቶችን በመቀየርና በማሻሻል ረገድ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይገባል ብለዋል።

አቶ ደመቀ፤ በኢትዮጵያ የወሳኝ ኩነት መረጃን በቴክኖሎጂ በመታገዝ በዘመናዊ መንገድ መያዝ እንደተጀመረ ገልጸው፤ ሀገሪቷ የወሳኝ ኩነት ዘርፍን ለሌሎች አገልግሎት ጭምር እየተጠቀመችበት መሆኗንም ጠቅሰዋል።የሥነ ሕዝብ መረጃን በጥራት ለማከናወን የስታቲስቲክስ አገልግሎትን በቴክኖሎጂ መምራት እንደሚገባም ተናግረዋል።

ልማትና ኢኮኖሚያዊ እድገት የዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ይጨምራል ያሉት አቶ ደመቀ፤ ምንም እንኳን እንደ አፍሪካ የተለያዩ ተግዳሮቶች ቢኖሩም የዲጂታል መረጃንና ቴክኖሎጂን ለልማት ጥቅም ላይ ለማዋል አዳዲስ እድሎችን መጠቀም እንደሚገባ አስታውቀዋል።በአፍሪካ አህጉር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የቁልፍ፣ "የመረጃ ባለድርሻ አካላት" ውጤታማ ሥራን ለማገዝ ጉባዔው አስቻይ እንደሆነም ጠቅሰዋል።

የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ፔድሮ በጉባዔው ላይ እንደገለጹት ፤ ባለፉት ዓመታት በአፍሪካ ከፍተኛ አመራሮች ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠታቸው የዘርፉ ባለሙያዎችን ማብቃት ተችሏል። የቫይታል ስታስቲክስ ሥርዓትን ለመዘርጋት፣ የዜጐችን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ለማስከበር፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያስችል የሥነ ሕዝብ መረጃ እንዲኖር ጉባኤው ያግዛል።

እንደ አፍሪካ ያሉ ተግዳሮቶችንና መልካም ተሞክሮዎችን መጋራት የጉባዔው አንዱ አካል እንደሆነ ገልጸው፤ የ2030 ዘላቂ የልማት ግብ እንዲሁም "የምንፈልጋት አፍሪካ" ለሚለው 2063 አጀንዳ ጋር ትስስር ያላቸው ሀሳቦች ተንጸባርቀው ቀጣይ አቅጣጫዎች የሚቀመጡበት ጉባዔ እንደሚሆን አስታውቀዋል።

ጉባዔው "ቀጣናዊ ትስስርን ለማጠናከርና ለመደገፍ በአፍሪካ የመረጃ አያያዝን ማዘመን" በሚል መሪ ቃል ከጥቅምት 14 እስከ ጥቅምት 18 ቀን 2015 ዓ.ም በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን እየተካሄደ ይገኛል።

# መከላከያ ሠራዊቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አሁን ያለው ትውልድ ታሪክን መማሪያ አድርጎ በመመዝገብ ለትውልድ ለማስተላለፍ ቆርጦ የተነሳ መሆኑ ይህን ዐውደ ርዕይ የተለየ ያደርገዋል ብለዋል።

የቀደሙት ለሀገር የከፈሉትን ዋጋ ክብር በመስጠት በቀጣይም ጠንካራና የበለጸገች ኢትዮጵያን በመገንባት ለትውልዱ ማስተላለፍ አለብን ያሉት ሚኒስትሩ፤ ታሪኮቻችን መማሪያዎቻችን በመሆናቸው ሰንዶ ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን ትልቅ ሙዚየም በመገንባት ትውልድ እንዲማርባቸው እየሠራን ነው ሲሉ አብራርተዋል።

የመከላከያ ቀንን በማስመልከት በመከላከያ ጠቅላይ መምሪያ የተዘጋጀና ከጥቅምት 14 እስከ 18/2015 ዓ.ም የሚቆይ ከ1900 ዓ.ም ጀምሮ የመከላከያ ሚኒስትሮችና ኤታማዦር ሹሞች ፎቶግራፍ የሚያሳይ የፎቶ ዓውደ ርዕይ በትናንትናው ዕለት በመከላከያ ሚኒስትሩ ተመርቆ ተከፍቷል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕዝባዊ፣ ከሩቅ የሚፈራና የተከበረ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ተገንብቷል !

በዱር በገደል ተንከራቶ ፣ አጥንቱን ከስክሶ፤ ደሙን አፍስሶና ህይወቱን ሰውቶ ንጹህ አየር እንድንተነፍስ፤ በሰላም ወጥተን እንድንገባ፣ የሀገር ሉዓላዊነት እያስከበረ የሚገኘው ጀግናው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ነው።

የመከላከያ ሰራዊቱ የግንባታ አቅጣጫ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅነት የሚመጥን፤ በቀጣናው ላለበት ከፍተኛ ኃላፊነት ብቁ የሆነ፣ የሕዝብ አመኔታን የተጎናፀፈ፣ ወታደራዊ ዕውቀትና ክህሎትን የጨበጠ፣ በፈጠረው አስተማማኝ ዝግጁነት ጦርነትን በሩቁ ማስቀረት የሚችል፣ በዓለም አቀፍ ሰላም ማስከበር ተገቢውን ሚና የሚጫወት ኃይል የመፍጠርን ራዕይ የሰነቀ ነው። ይህንኑ ራዕዩን እውን እያደረገና በተጨባጭም እያረጋገጠ ይገኛል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ሰራዊት ከኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች አብራክ የወጣና ኢትዮጵያን የሚመስል ለሕዝብ ደኅንነትና ለሀገር ሉዓላዊነት የአካልና የህይወት መስዋዕትነት የሚከፍል ብሔራዊ ኃይል ነው፡፡ ይህ የሕዝብ ልጅ የሆነው ሠራዊታችን ከሕዝቡ ጋር ያለውን ትስስርና አንድነት በማጠናከር የሕዝቡን የባለቤትነት ስሜት ይበልጥ እያጎለበተ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ግንባታ ከፍተኛ አቅም ተፈጥሯል፤ ከሩቅ የሚፈራ፣ በብቃቱ የተመሰከረለት ፤ ሳይዋጋ የሚያሸንፍ መከላከያ ሠራዊት ሆኗል። ይህም መከላከያ ሠራዊቱን እንኳን ኢትዮጵያን አፍሪካን ጭምር የሚያኮራ ያደርገዋል።

ከኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች አብራክ የተገኘው ሠራዊት ከተቋቋመበት ዓላማ ጎን ለጎን ከበቀለበት ሕዝብ ጎን በመቆም ማኅበራዊ ኃላፊነቱን በተለያየ መልኩም ሲወጣ ቆይቷል። አሁንም እየተወጣ ይገኛል። በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች ግንባር ቀደም በመሆን፣ የአቅመ ደካማ ዜጎችን መኖሪያ ቤት በመገንባት፣ በእርሻ ወቅት አርሶ አደሩን በአጨዳውና በሰብል ስብሰባ በማገዝ ፤ ሰብል ሊያጠፋ የመጣበትን አንበጣ በማባረር ጭምር የሕዝብ አለኝታ መሆኑን ደግሞ ደጋግሞ አረጋግጧል። የሕዝብ ሃዘን ሃዘኑ፤ የሕዝብ ደስታ ደስታው የሆነው ይሄ ሠራዊት የሕዝብን ችግሮች የራሱ ችግሮች አድርጎ እርሱ እየተራበ ሌላውን እየመገበና እርሱ እየሞተ ሌላውን እያኖረ ኖሯል።

ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለዓባይ ግድብ በእውቀት፣ በገንዘብ እና በጉልበት ድጋፍ ሲያደርጉ የመከላከያ ሰራዊቱ ግን በበረሀ ላይ ቀን በጸሀይ ሀሩር እየተቃጠለ፤ ሌሊት በውርጭና ቁር እየተጠበሰ ግድቡን ሲጠብቅ ውሎ ያድራል። ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ በላይ ከስድስት እና ሰባት ጊዜ በላይ ደመወዙን በመስጠትና ቦንድ በመግዛትም ጭምር የቁርጥ ቀን ልጅ መሆኑን አስመስክሯል።

የመከላከያ ሠራዊቱ በስነምግባሩ አንቱ የተባለ፤ በብቃቱ የተመሰከረለት ጀግና ሠራዊት መሆኑን ከሀገር ውስጥ በተጨማሪ በሰላም ማስከበር በተሰማራባቸው ሀገሮችና የግዳጅ ቀጣናዎች ሁሉ አስመስክሯል። በብቃቱ ፣ በታማኝነቱ ፣ በስነምግባሩ እና በህዝብ አገልጋይነቱ በሰላም አስከባሪነት በተባበሩት መንግስታት ተመራጭ ሆኖ በሰራቸው የሰላም ማስከበር ስራዎች የእውቅና ሽልማት ጭምር ተችሮታል። አሁንም ይሄንኑ ክብሩንና ብቃቱን አስጠብቆ ቀጥሏል።

የሕዝብን ደኅንነት ለማረጋገጥ፤ የሀገራችንን አንድነት ለማስቀጠልና ሀገርን ከመፍረስ አደጋ በመታደግ ሠራዊታችን በተለያዩ ጊዜያት ከውስጥ እና ከውጪ ጠላቶቻችን ጋር ተጋድሎ በማድረግ አኩሪ መስዋእትነት ከፍሏል። አኩሪ ድሎችንም አስመዝግቧል። ለዚህ ታላቅ መስዋዕትነት ዕውቅና መስጠትና በክብር እንዲዘከር ማድረግ ይገባል።

የታሪክ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በ1983 ዓ.ም ጀምሮ እንዲፈርስ ፣ ክብሩና ዝናው ረክሶ እንዲፈረካከስ ተደርጎ መቆየቱ የሚዘነጋ አይደለም። የመከላከያ ሠራዊቱ ቁመናም በአንድ ብሄር አዛዥነትና የበላይነት ላይ የተመሰረተ እንጂ ኅብረ ብሄራዊ አልነበረም። ሀገሪቱ የባህር ኃይልም እንዳይኖራትና ሌላውም የመከላከያ ኃይል ጠንካራ ሆኖ እንዳይቀጥል ተደርጓል። ይሁን እንጂ በሀገራችን የመጣውን ለውጥ ተከትሎ የባህር ኃይሉም እንደገና እንዲደራጅ የመከላከያ ሠራዊቱም ኢትዮጵያን በሚመስልና በሚመጥን መልኩ ሆኖ ተደራጅቷል። ይህም በመሆኑ ዛሬ አሸባሪው ትህነግ ሁለት ሶስት ጊዜ ያደረገውን ወረራ በብቃቱ መመከትና መቀልበስ ችሏል።

ኢትዮጵያ የግዛት አንድነቷ በማንም እንደማይሸረፍ በመስዋዕትነት የሚያረጋግጥ ጀግና መከላከያ ሠራዊት ያላት ሀገር ናት። ይህንንም አሸባሪው ትህነግ ከታሪካዊ ጠላቶችና የኢትዮጵያን እድገት ከማይፈልጉ የውጭ ጠላቶች ጋር ሆኖ የተልዕኮ ውጊያ በገጠመበት ወቅት አስመስክሯል።

ቀደም ሲልም የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሚታወቀውም በዚሁ ጀግንነቱ ነበር። ይሄ ህዝባዊ ሠራዊት አሁንም ለሀገሩ ሉዓላዊነት ህይወቱን ሳይሰስት የሚሰጥ እና የሚያስከብር ሙሉ ብቃትና ዝግጁነት ያለው ነው። ዛሬም ነገም የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ህዝባዊ ፣ ከሩቅ የሚፈራና የሚከበር ሆኖ በጀግንነቱ ይቀጥላል። ዛሬም አኩሪ ተልዕኮውን በመፈጸም ታላቅ ሀገራዊ ኃላፊነቱን በብቃት እየተወጣ ይገኛል። ለዚህ ጀግና ሠራዊት ታላቅ ክብርና ምስጋና ያስፈልገዋል። ይገባዋል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# “ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ...”

ሶሎሞን በየነ

የትግራይ ሕዝብ እና ወራሪው እና አሸባሪው የትህነግ ቡድን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፤ቡድኑ ያለ ትግራይ ህዝብ፤ የትግራይ ሕዝብ ያለ ቡድኑ ከባህር እንደወጣ ዓሳ ማለት እንደሆነ አድርገው የሚያስቡ አሉ። በአንፃሩ የትግራይ ህዝብና የትህነግ ለየቅል ናቸው። ሁለቱን ነጥሎ ማየት ያስፈልጋል የሚል ሀሳብ የሚያነሱም ብዙዎች ናቸው። እንደኔ አመለካከት ሊጠናና ሊሰላ ወይም የመከራከሪያ ነጥብ ሊሆን የሚገባው የትግራይ ሕዝብ ለትህነግ ምን መሰዋት ከፈለ? በሌላ በኩል ደግሞ ቡድኑ ለትግራይ ሕዝብ ምን ጠቀመው? ወይም ምን አመጣለት? በሚለው ላይ ሊሆን ይገባል ባይ ነኝ።

በዚህ አጭር ጽሁፌ ይህንን ሀሳብ መንደርደሪያ በማድረግ ትህነግ በ1969 ዓ.ም በደደቢት በረሃ ከተመሰረተ ጀምሮ አሁን እስካለንበት ወቅት ድረስ ያለውን እውነታ በወፍ በረር ለማየት እሞክራለሁ።

“ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል እድሜ ልክ ሲያለቅስ ይኖራል” እንደሚባለው ለኔ የትግራይ ህዝብ ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ነው። ምክንያቱም በሴራ እና በበታችነት ስሜት በ1960ዎቹ መጨረሻ ወደ ጫካ የወረደው አሸባሪው የትህነግ ቡድን ከጥንስሱ ጀምሮ በትግራይ እናቶች የማህፀን ክፋይ ደም የጨቀየ ነው።

በዚያ በደርግ ዘመን ይደርስ የነበረውን ግፍና መከራ ለመታገል ብሎም ከቀይና ነጭ ሽብር ሰይፍ ለማምለጥ በአራቱ የትግራይ ማዕዘን ወደ በረሃ ከጎረፉ የትግራይ ወጣቶች ውስጥ ሕዝባዊ አመለካከት የነበራቸውን ከትግራይ ህዝብ አብራክ የወጡ የህዝብ ልጆችን በሴራ በማስወገድ ጸረ- ህዝብነቱን አሃዱ ብሎ የጀመረ አሸባሪ ቡድን ነው ።

ቡድኑ በዚህ ፀረ-ህዝብነቱ ብሩህ አዕምሮና ህዝባዊ አመለካከት እንዲሁም ተሰሚነትና ተደማጭነት ያላቸው ታጋዮች ቀጣይ ስጋት ይሆናሉ በሚል በስፋት መግደሉ ይነገራል። በጦርነቱ ከሞቱት ይልቅ በቡድኑ ሴራ ለህልፈት የተዳረጉ ይበልጣሉ የሚሉም ብዙ ናቸው። በ17 ዓመቱ የትጥቅ ትግሉም የትግራይ እናቶች ከ60 ሺ በላይ የማህጸናቸውን ፍሬ ገብረዋል።

ለትግራይ እናቶች ሾተላይ የሆነው የጁንታው ቡድን በ1977 በአገሪቱ የተከሰተውን ድርቅና ይህን ተከትሎ የተፈጠረው ረሃብ የትግራይን ህዝብ እንደቅጠል ሲያረግፍ ቡድኑ ሰብአዊ ድጋፍና እርዳታ ለህዝቡ እንዳይደርስ በማድረግ የትግራይ ህዝብ ለከፋ እልቂት ዳርጓል ፤ ህዝቡ ተስፋ ቢስ እንዲሆን በማድረግ ወደ ጦር ሜዳ ገብቶ የሳት እራት እንዲሆን ሰርቷል። ለእርዳታ የመጣ ገንዘብን ለጦር መሳሪያ መግዣ ከማዋል ጀምሮ፤ የእርዳታ አቅርቦቶችን በመሸጥ ለተመሳሳይ ተግባር አውሏል።

እንዲሁም የማፊያው ቡድን በሸረበው ሴራ የደርግ መንግስት ለገበያ በወጣው በሃውዜን ህዝብ ላይ የቦንብ ናዳ እንዲያወርድ ፤ እልቂቱን በድብቅ በመቅረጽ የወገኖቹን ደም ለፕሮፓጋንዳ ያዋለ የጭራቆች ስብስብ ነው። በጥቅሉ የማፊያው ቡድን በትግራይ እናቶች ማህጸን ፍሬ በሆኑ ለጋ ወጣቶች እየቆመረ ከ17 ዓመታት የትጥቅ ትግል በኋላ አራት ኪሎ ቤተ መንግሥትን መግባት የቻለ ነው።

የማፊያው ቡድን በትረ ስልጣኑን ከተቆጣጠረ በኋላ ስልጣን ላይ በነበረበት 27 ዓመታት ለትግራይ ሕዝብ ምን አመጣለት? ብለን ስንጠይቅ የአንድ ጎጥ ተወላጆች ባንኩን፣ ታንኩን ፣ ንግዱን፣ መርከቡን፣ ፕሌኑን ወ.ዘ.ተ ተቆጣጥረው የአገሪቱን አንጡራ ሀብት ሲዘርፉ ነበር። ነገር ግን ልጆቻቸውን የጦር ሜዳ ሲሳይ አድርገው ለዚህ ስልጣን ያበቋቸው የትግራይ እናቶች የሚጠጡት ንጹህ ውሃ እንኳን አላገኙም። በስመ ትግሬ የአንድ ጎጥ ተወላጆች አገር ሲዘርፉ ልጇን በጦርነት የገበረች የትግራይ እናት ግን የልጇን ፎቶ ታቅፋ ነው የቀረችው።

በጥቅሉ በትህነግ የአገዛዝ ዘመን የትግራይ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ የተለየ ያገኘው ጥቅም የለም። ይልቁንም በጨቋኝና በተጨቋኝ ትርክት የትግራይ ሕዝብ ከሌሎች እህት ወንድም ከሆኑ ህዝብ ጋር ተስማምቶ እንዳይኖር ሴራ እየሸረበ በጎሪጥ እንዲተያይ ሲያደርግ ቆይቷል።

ቡድኑ ቀደም ባለው ጊዜ ባንኩን፣ ታንኩን ፣ ንግዱን፣ መርከቡን በእጁ ስር አድርጎ ተቆጣጥሮ በነበረበት ወቅት ዞር ብሎ ያላየውን የትግራይን ህዝብ ከጠዋት ከማታ ሳያስበው ከአራት ኪሎ ቤተመንግስት ሲነቀል፤ የአማዞን ጫካ የአለም ሳንባ እንደሆነ ሁሉ ትህነግ በትግራይ ሕዝብ ጉያ ተደብቆ ልትቋረጥ ያለችውን እስትንፋሱን ማቆያ ጫካ አድርጎ እየተጠቀመበት ይገኛል።

ይህ የሽብር ቡድን በተደጋጋሚ መንግሥት ለሰላም የዘረጋውን እጅ በማጠፍ “ከፈላጭ ቆራጭነቴ ተነስቼ እንዴት እኩል እታያለሁ” በሚል ትዕቢት ዳግም የትግራይ እናቶችን የማህጸን ፍሬ የሆኑ ህጻናትን ጭምር በአደንዛዥ እጽ እያሳበደ የእሳት እራት እያደረገ ይገኛል።

በዚህም የጁንታው አመራሮች ልጆቻቸውን በአሜሪካና አውሮፓ በቅንጡ ትምህርት ቤት እያስተማሩ የአገር መከላከያ ሰራዊትን ከጀርባው ወግቶ ባስጀመረው የሰሜኑ ጦርነት የረገፉ የትግራይ የድሃ ልጆችን ቤት ይቁጠረው።

እንዲሁም ማንም ቤተሰብ ልጁን ለትህነግ የጦር ሜዳ ሲሳይ አድርጎ ካልገበረ የሰብአዊ እርዳታም ሆነ ድጋፍ እንደማያገኝ በምርኮ የተያዙ የክልሉ ተወላጆች ሲናገሩ ተደምጠዋል። የሰብአዊ ድጋፍና እርዳታን ለጦርነት በማዋል የትግራይ ሕዝብ በርሃብ አለንጋ እንዲገረፍ በማድረግ ህዝቡ ተስፋ ቆርጦ ወደ ጦርነት እንዲማገድና እንዲያልቅ እያደረገ ይገኛል።

ለአብነት በቅርቡ የጥምር ጦሩ ዘልቆ በገባባቸው በትግራይ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች ህዝቡ የሚበላው አጥቶ ፆሙን እያደረ ነገር ግን ቡድኑ ለጦርነት ሲል ደብቆ ያስቀመጠው የዩኤስ ኤይድ እርዳታ ተገኝቶ ለሕዝቡ ሲከፋፈል ተመልክተናል።

በጥቅሉ የማፊያው ቡድን ከጥንስሱ ጀምሮ ለአምስት አስርት ዓመታት የትግራይን ህዝብ የጦር ሜዳ ሲሳይ ከማድረጉ ባሻገር በተለይ የሰሜኑ ጦርነት ከተቀሰቀሰ ጀምሮ የትግራይ ህዝብ ከአለም ጋር እንዳይገናኝ እና ሀሳብ እንዳይቀያየር አፍኖ ይዞ በትምህርት፣ በቴክኖሎጂ፣ በልማት ወ.ዘ.ተ ወደ ኋላ በማስቀረት ወደ ድንጋይ ዘመን ቀይሮታል ቢባል ማጋነን አይሆንብኝም።

ታዲያ የትግራይ ሕዝብ ለዘመናት ውድ ልጆቹን እና ሕይወቱን ለትህነግ ገብሮ በምላሹ ቡድኑ ምን ወረታ ከፈለ ብለን ስንጠይቅ? ምላሹ አይደለም ለትግራይ ህዝብ ለሌሎች እህትና ወንድም ህዝቦች የእግር እሳት ነው የሆነው። በተለይ በስልጣን ዘመኑ ህዝባዊ አመለካከት ያላቸውን የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ጥፍር ነቅሏል፣ አኮላሽቷል አገር ዘርፏል፣ ከዷል... በጥቅሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ህልቆ መሳፍርት የሌለው በደል አድርሷል። ሆኖም ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች በላይ ቡድኑ ለዘመናት የነገደው በየትግራይ ሕዝብ ደም፣ ስጋና አጥንት ላይ ነው።

የትግራይ ህዝብ ይህን የሽብር ቡድን ከሌሎች እህት ወንድሞቹ ጋር ድርና ማግ ሆኖ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከጫንቃው አሽቀንጥሮ የሚጥልበት ጊዜው አሁን ነው። የሽብር ቡድኑ “የእናት ጡት ከጣለ ህጻን ጀምሮ ምርኩዝ ይዞ መንቀሳቀስ እስከሚችል የ75 እና 80 ዓመት አዛውንት ድረስ ያለ ማንኛውም የትግራይ ተወላጅ ጦር መሳሪያ ባይኖርህ ድንጋይ ይዘህ በእህት ወንድሞችህ ላይ ወደ ጦር ሜዳ ዝመት” ብሎ የጎሰመውን የጦርነት ነጋሪት የትግራይ ህዝብ “አሻፈረኝ” በማለት የጥፋት ቡድኑ መንግሥት ወደ አቀረበው ሰላማዊ ድርድር እንዲቀርብ ግፊት ማድረግ፤ አልያም ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝብ እህት ወንድሞቹ ጋር በመሆን ለዘመናት በደሙ የነገደውን “የትግራይ እናቶች ሾተላይ” ግብዓተ መሬቱን መፈጸም ይኖርበታል።

# ነፃ ሃሳብ

## የሚበረታታው የትምህርት ሚኒስቴር የለውጥ መንገድ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ትምህርት ሚኒስቴር ከሰሞኑ በተማሪዎች የአፈታተን ሂደት ላይ አዲስ አቅጣጫ አስቀምጧል። የፈተና አሰጣጡ በተለየ መልኩ በዩኒቨርሲቲዎችና በዩኒቨርሲቲ መምህራን የሚሰጥበትን ሁኔታ አመቻችቶ ተማሪዎችም በዛ ሁኔታ ፈተናቸውን ወስደዋል። ይሄ መሆኑ ከመማር ማስተማር ስርአቱ ባሻገር በትምህርት ጥራት ላይ የሚፈጥረው የራሱ የሆነ አዎንታዊ በረከት አለው ።

ቀደም ባለው ጊዜ የነበረው የፈተና አሰጣጥ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ሁላችንም የምናውቀው ነው። ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲ መጥተው በአንድ ቦታ ላይ ሲፈተኑ የሚኖረው ጠቀሜታ ሰፊ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ ። እንዲህም በሆኖ አንዳንድ ተማሪዎችና የተማሪ ወላጆች በአዲሱ የትምህርት ሚኒስቴር አቅጣጫ ላይ ቅሬታዎችን ቢያሰሙም ብዙሀኑ ተማሪና የተማሪ ወላጆች ግን አዲሱን የአፈታተን ስርአት በይሁንታ ተቀብለውታል።

ሀገር ከምትበለጽግባቸውና ዘመናዊነትን ከምትላበስባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ትምህርት ነው። ትምህርት ስንል ሰፊ ሀሳብ ነው። ከዚህ እንደባህር ከሰፋ ሀሳብ ውስጥ ተማሪና የትምህርት ጥራትን ብናነሳ እንኳን ብዙ ሀሳቦችን ማንሸራሸር እንችላለን። ትምህርት ሀገር፣ ትውልድ፣ ስልጣኔ ከሚፈጠርባቸው መንገዶች ውስጥ ዋነኛው ነው ካልን የፈተና አሰጣጣችንና የአፈታተን መንገዳችን ምን ይመስላል? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ይኖርብናል።

ያለፉትን ጥቂት አመታት መለስ ብለን ብናይ በትምህርቱ ዙሪያ በርካታ ቅሬታዎች እንደነበሩ እንደርስበታለን። ከፈተና በፊትና ከፈተና በኋላ የሚነሱ አንዳንድ አሉባልታዎች የተማሪዎችን ስነ ልቦና ከመጉዳት ባለፈ በትምህርት ጥራት ላይ የሚፈጥረው የራሱ የሆነ ተጽእኖ ነበረው። አንዳንድ ኃላፊነት በማይገባቸው ሰዎች መሪነት በትምህርቱ ሴክተር ላይ ይሄ ነው የማይባል የአሉባልታ ጦርነት ተከፍቶበታል። መንግስት ይሄን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ከወሰዳቸው ርምጃዎች ውስጥ አንዱ ደግሞ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ውስጥ እንዲፈተኑ ማድረግ ነው።

ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ውስጥ መፈተናቸው የትምህርት ጥራትን ከመጠበቅና የሚነሱ አንዳንድ ቅሬታዎችን ከማስቀረት ባለፈ የራሱ የሆነ ጥቅም አለው። ተማሪዎች በውጤታቸው አማካኝነት ወደ ተመደቡበት ዩኒቨርሲቲ ከመግባታቸው በፊት ዩኒቨርሲቲ ምን እንደሚመስል ያያሉ። ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ለሚገጥማቸው ማናቸውም ነገሮች ቀድመው እንዲዘጋጁ እድል ይሰጣቸዋል።

**ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ውስጥ መፈተናቸው የትምህርት ጥራትን ከመጠበቅና የሚነሱ አንዳንድ ቅሬታዎችን ከማስቀረት ባለፈ የራሱ የሆነ ጥቅም አለው። ተማሪዎች በውጤታቸው አማካኝነት ወደ ተመደቡበት ዩኒቨርሲቲ ከመግባታቸው በፊት ዩኒቨርሲቲ ምን እንደሚመስል ያያሉ። ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ለሚገጥማቸው ማናቸውም ነገሮች ቀድመው እንዲዘጋጁ እድል ይሰጣቸዋል**

ከተለያዩ ቦታ ከመጡ ተማሪዎች ጋር ለልምድ ልውውጥ እድል ይከፍትላቸዋል። ይሄ ትንሹ በረከቱ ነው። በዋናነት ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ እንዲፈተኑ የተደረገበት ምክንያት የኩረጃና የአንዳንድ ግለሰቦችን ወገንተኝነት ለማስቀረት ነው። ኮርጆ ያለፈ ተማሪ አይደለም ለሀገር አይደለም ለወገኑ ለራሱ መሆን አይቻለውም። እንደ ወንፊት እያነፈሰ ስንዴውን ከእንክርዳዱ የሚለይ የትምህርት ስርአት ያስፈልገናል። ኩረጃን የሚጸየፍ ተማሪና ማህበረሰብ መፍጠር የትምህርት ሚኒስቴር ተቀዳሚ ስራው ነው። ለዚህም በመማር ማስተማሩ ላይ አስተማማኝ ህግና ደንቦችን ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

በአጉል የትምህርት ስርአት ሀገር ነው የሚፈርሰው…ትውልድ ነው የሚመክነው። ሁልጊዜም ለሀገራችን የተሳለውን ነገር ማሰብ ይኖርብናል። ሀገር የምትገነባው ጥራት ባለው ትምህርትና ጥራት ባላቸው ተማሪዎች ነው። ዛሬ ላይ በየህክምና ተቋሙ፣ በየሆስፒታሉ፣ በየጤና ጣቢያው በህክምና ስህተት የምንሰማቸው ሞቶችና የአካል መጉደሎች እኮ ጥራት በሌለው ትምህርትና ጥራት በሌላቸው ተማሪዎች የተፈጠረ ነው።

ዛሬ ላይ በምህንድስናው ዘርፍ እየታዩ ያሉ ክፍተቶች ኩረጃ የፈጠራቸው እንከኖች ናቸው። ችግሮቻችንን ለማሸነፍ በትምህርት ዘርፉ ላይ ይሄ ነው የሚባል ለውጥ ማምጣት ይኖርብናል። የትምህርት ዘርፉን አስተማማኝ ሳናደርግ የምንሄድበት መንገድ ሩቅ አያደርሰንም። ለጋራ ጥቅም በጋራ ስናብር ሀገር እየሰራን እንደሆነ ማሰብ አለብን። ሁሉም ነገር እውቀትን መሰረት አድርጎ የቆመ ነው። እውቀትን መሰረት ያደረገ ተማሪና ማህበረሰብ ካልፈጠርን ሀገራችንን ለውድቀት እየዳረግናት እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል።

ሀገራችን በሁሉም መስክ ጥራት ያላት እንድትሆን ጥራት ያለው ትምህርትና፤ ጥራት ያላቸው ተማሪዎችና መምህራኖች ያስፈልጓታል። የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ መነሻውና መድረሻው የተማረ የሰው ሀይል ነው። የተማረ የሰው ሀይል ደግሞ ሊገነባ የሚችለው ጥራት ባለው ትምህርት ነው። በአንድ ሀገር ሁሉንም መሆን የሚችሉ ነገሮች ጥቂቶች ናቸው። ትምህርትን ብንወስድ ሁሉም ቦታ ላይ ሁሉንም ነገር ሆኖ ልናገኘው እንችላለን። ካለ ትምህርት የተገነባ ኢኮኖሚ፣ የተመሰረተ ፖለቲካ፣ የቆመ ማህበራዊ መስተጋብር የለም።

ካለእውቀት የሚፈጠር ትውልድ፣ የሚመጣ ለውጥ የለም። ጠንካራ የትምህርት ስርአት ሁሉንም መሆን የሚችል ነው። በዚህ በአንድ ሀገር ላይ ሁሉንም ለሆነ ትምህርት ምን እያደረግን ነው የሚለው ጥያቄ መንግስትም እንደመንግስት እኔና እናተም እንደ ዜጋ ልንመልሰው የሚገባ ጥያቄ ነው። ለአንድ ጊዜ አለምን መለስ ብለን ብንቃኛት በትምህርት የቆነጀች ሆነን እናገኛታለን። ለአፍታ ስልጡን ሀገራትን ብናስባቸው የጥንካሬአቸው ምንጭ ጥራት ያለው የትምህርት ስርአት እንደሆነ እንደርስበታለን።

እኛ ሀገር ሲሆን ግን ሌላ ነው። ትምህርት ለእድገት ዋነኛ ነገር እንደሆነ እናውቃለን ጥራት ያለው ትምህርት ለማምጣት ስንጥር ግን አይታይም። በራሱ የሚተማመን እውቀትን መሰረት ያደረገ ተማሪ ገና አልፈጠርንም። ብዙ ክፍተቶቻችን ለትምህርት ከሰጠነው አናሳ ግምት የተነሱ እንደሆኑ ለማወቅ ጠቢብ መሆን አይጠበቅብንም። በየአመቱ ከትምህርት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ከተማሪና ከወላጅ ቅሬታ እንደተነሳ ነው። ከመንግስትም ማብራሪያ ሲሰጥ ማየት አዲስ ነገር አይደለም።

በትምህርት ዘርፉ ላይ ጥያቄ የማይፈጥሩ አስተማማኝ ስራዎች ይጠበቁብናል። አሁን ላይ የታየው አዲስ አካሄድ የምንናፍቀውን ለውጥና አዲስነት ይሰጠናል ብለን እናምናለን። እስከዛሬ ለስህተት በተጋለጡ የመፈተኛ ቦታዎች ተማሪዎቻችንን ስንፈትን ነበር። በሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ላይ ፈታኝ ሆነው የተመደቡ መምህራኖች ነበሩ። እኚህና የመሳሰሉት አካሄዶች ለውጥ ሳያመጡልን በትምህርት ጥራቱ ላይ ጥያቄን ፈጥረው ሰንብተዋል።

ጥራት ያለው ትምህርት ጥራት ያለው ማህበረሰብን ይፈጥራል። ጥራት ያለው ማህበረሰብ ደግሞ ጥራት ያላትን ሀገርና ትውልድ መገንባት ይችላል። እናም የትምህርት ሚኒስቴር ለትምህርት ጥራት ቅድሚያ ሰጥቶ መስራቱ ሊያስገርመን አይገባም። ሀገራችን በሁሉም ዘርፍ የእኛን ተሳትፎ የምትፈልግበት ጊዜ ላይ ነን። በትምህርቱ ላይ አስተማማኝ ለውጥ ካመጣን በሌሎች ጉዳዮች ላይ መግባባት አያዳግተንም።

ያልተማረ ጭንቅላት፣ እውቀትንና ምክንያታዊነትን ያልተላበሰ አእምሮ መግባባት ይቸግረዋል። የዛሬ ችግሮቻችን ከዚህ እውነት ውስጥ የሚመዘዙ እንደሆኑ ማሰብ እንችላለን። በሁሉም ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን ጥራት ያለው ትምህርት ላይ ልንረባረብ ይገባል። እንደ ተማሪ፣ እንደ ዜጋ መንግስት ለሀገር ጥራት በሚወስዳቸው አንዳንድ ማሻሻያዎች ላይ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ ጥራት ያላትን ሀገር በመፍጠር ሂደት ላይ ልንሳተፍ ይገባል።

አንዳንድ ነገሮች የተለየ አቅጣጫ ይፈልጋሉ። አለም ከፍጥነት አቅጣጫ የተሻለ ነው የሚል አባባል አላት። እንደ መንግስት፣ እንደ ዜጋ አቅጣጫዎቻችንን በመቀየር የምንቀይራቸው ብዙ ነገሮች አሉ። አሁን ላይ የሚያስፈልገን ምንም ሳይሆን የአቅጣጫ ለውጥ ብቻ ነው። በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በጤናው፣ በትምህርት፣ በትራንስፖርት ዘርፉ በሁሉም ነገር ላይ የአቅጣጫ ለውጥ ያስፈልገናል። የተራመድንባቸው መንገዶች አዲስ ነገርን አልሰጡንም። የአቅጣጫ እሳቤ በህይወት ውስጥ የትም ቦታ የሚሰራ ነው።

ሰው ከለመደውና ለውጥ ሊያመጠለት ካልቻለ ዘልማድ መውጣት መቻል አለበት። ለተከታታይ አመታት በአንድ አይነት የትምህርት አሰጣጥ ላይ ተሳትፈን ኩረጃን፣ አሉባልታን ማስቀረት አልቻልንም። ለተከታታይ አመታት በአንድ አይነት እሳቤ ውስጥ ቆመን የምንፈልገውን የትምህርት ጥራት አላሳካንም። ይባስ ብሎ ችግሮቻችን ከአመት አመት እየተባባሱ በመማር ማስተማር ስርአቱ ላይ እንቅፋት ሲፈጥሩ ነበር። አሁን የአቅጣጫ ለውጥ ነው ያደረግነው። ይሄ የአቅጣጫ ለውጥ የታሰበለትን አላማ እንደሚያመጣ እሙን ነው።

ከዚህ በፊት የፈተና ስርቆት ነበር። አካባቢን ለመጥቀም ሲባል በትውልድ ላይ በደል የሚፈጽሙ አንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች ነበሩ። ፈተና ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ ሲጓጓዝ የሚፈጠር ችግር ነበር። የአሁኑ የትምህርት ሚኒስቴር የአቅጣጫ ለውጥ ግን እነዚህን ሁሉ ችግሮች የሚያስቀር ነው። መንግስት የዚያን ሁሉ ተማሪ ወጪ ችሎ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ እንዲፈተኑ ያደረገው ከጉዳቱ ይልቅ ጥቅሙ እንደሚያመዝን ስለተረዳ ነው።

ለተማሪ ትራንስፖርትና ምግብ ተብሎ ከመንግስት ካዝና የወጣው ገንዘብ ብዙ ስራዎችን የሚሰራ ቢሆንም መንግስት ይሄን ውሳኔ የወሰነው ለትምህርት ጥራት ካለው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ እንደሆነ ማሰብ አይከብድም። አንዳንድ አቅጣጫዎች እስኪለመዱ ድረስ ዋጋ ያስከፍላሉ። ከተለመዱ በኋላ ግን ዋጋቸው የላቀ ነው። በዚህ የትምህርት ሚኒስቴር የአቅጣጫ ለውጥ ተጉዘን ጥራት ባለው ትምህርት ጥራት ያላቸውን ዜጎች እንደምናፈራ አምናለው።

አዳዲስ ነገሮችን መለማመድ አለብን። በአንድ አቅጣጫ ብቻ መጓዝ አዲስ ነገር አያስገኝልንም። አሁን ላለችው ኢትዮጵያ የሀሳብ ለውጥ፣ የፍጥነት ለውጥ ባጠቃላይ የአቅጣጫ ለውጥ ነው የሚያስፈልጋት። በተመሳሳይ ፍጥነት፣ በተመሳሳይ መንገድ ላይ ተጉዘን ሩቅ መሄድ አንችልም። ያልሄድንባቸውን ሌሎች መንገዶች እንፈልግ። ባልሄድንባቸው ሌሎች መንገዶች ላይ እንራመድ።

ለችግሮቻችን መፍትሄ የምንሰጠው የአቅጣጫ ለውጥ ስናደርግ ነው። ፖለቲካዊና ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊም ተግዳሮቶቻችን እጅ የሚሰጡን ከተለመደውና ከደጋገምነው አዲስ ነገር ከሌለው አሮጌ ልማድ ስንወጣ ነው። በእኛ ሀገር ለብዙ ዘመናት ሳይቀየሩ በአንድ አይነት አቅጣጫና አስተሳሰብ ስር የሰደዱ ነገሮች ብዙ ናቸው። በአንድ አይነት ሀሳብ፣ በአንድ አይነት መንገድ ላይ ተጉዘን ለውጥ ማምጣት አንችልም። ትንሽ ዘወር ማለት አለብን።

አዲስ ነገር መነሻቸው አዲስ አስተሳሰብ ነው። አዲስ ሀገር ለመፍጠር አዲስ መንገድ ያስፈልገናል። አዲስ መንገድ ደግሞ በአዲስ አቅጣጫ የሚገኝ ነው። ትምህርት ሚኒስቴር የሀገር ዋልታና ማገር በሆነው የትምህርት ስርአት ላይ ለውጥ ለማምጣት ብዙ ለፍቷል። የትምህርት ስርአቱን ከመቀየር ጀምሮ፣ መማሪያ መጽሀፎችን በማሻሻል፣ የመምህራኖችን የትምህርት ደረጃ በማጤንና ለለውጡ ይጠቅማሉ ያላቸውን ሁሉ አድርጓል። በዚህ ሁሉ አዲስ ሂደት ውስጥ የሚመጣውን ለውጥ በጋራ የምንጠብቀው ይሆናል። ካሳለፍናቸው አንድ አይነት ሁኔታዎች የተሻለ ትምህርትና ተማሪን እንደምናገኝ ግን የታመነ ነው። በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ፈተና መስጠትን የትምህርት ጥራትን ከማምጣት አኳያ ብቻ ብናየው መልካም ነው። ከዚህ ውጪ ምንም ሊሆን አይችልም።

ልክ እንደ ትምህርት ስርአቱ ሁሉ የአቅጣጫ ለውጥ በማድረግ ልንቆጣጠራቸው እየቻልን ያልተቆጣጠርናቸው ችግሮቻችን ብዙ ናቸው። አንዳንድ ነገሮች ማሰብ ብቻ ነው የሚፈልጉት። አንዳንድ ነገሮች ከተለመደው ወጣ ብለን ስንከውናቸው ልክ ይሆናሉ። ያቃተን ትንሽ ማሰብና..ትንሽ ዞር ማለት ነበር። አሁን ዞር ብለናል.. ጣጣዎቻችን እጅ እንደሚሰጡን እናምናለን። ሀገራችን የቀድሞ ክብሯን፣ የምታገኘው በጨዋነት ነው። ጨዋነት ያምርብናል፤ ውበታችን ነው። ትንሽ በማሰብ…ትንሽ ዞር በማለት የራቀንን ጨዋነት እንመልስ። የሸሹንን ጸጋዎቻችንን እንመልስ። በመኮረጅና በማስኮረጅ የሚያድግ ሀገር የለም። ሀገር ልታድግ የምትችለው የሚገባውን ባገኘ ተማሪና ዜጋ ነው። የልፋታችንን ብቻ በማግኘት ለሀገራችን ውለታ እንዋል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ትውልድን በቴክኖሎጂ የማነፅ ግብ- የኢትዮ ቴሌኮም ድርሻ




ዳግም ከበደ

ዓለም በሳይንስና ቴክኖሎጂ የምርምር ውጤቶችና ግኝቶች እየተመራች ነው። ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች በዚሁ ዘርፍ መመራት ከጀመሩ ከፍለ ዘመን ሊቆጠር ምንም ያህል አልቀረውም። አገራት ኃያልነታቸውን በቴክኖሎጂና የሳይንስ ምርምር ውጤቶች ላይ ተመርኩዘው እየገነቡ ናቸው፣ ወታደራዊ ጡንቻዎቻቸውን የሚለኩት በዚሁ ዘርፍ ባስመዘገቡት ስኬት ልክ ሆኗል።

በሰው ልጅ ጉልበት አይሳኩም የተባሉ ታላላቅ ፕሮጀክቶች ብሩህ የመፍጠር አቅም ባላቸው ጥቂቶች በተፈለሰፉ ቴክኖሎጂዎች እውን ሲሆኑ አይተናል። አሁን ሁሉም ነገር በቴክኖሎጂና ረቂቅ ሳይንሳዊ ጉዳዮች ይመራል። ለዚህም ይመስላል አዲሱ ትውልድ ከዚሁ ጋር በተያያዙ እውቀቶች እንዲበለፅግ የሚፈለገው።

ምድራችን በሉላዊነት (globalization) መርህ እየተመራች ነው። ለዚህ ደግሞ ዲጂታል ቴክኖሎጂ፣ በይነ መረብ እና መሰል የግንኙነት መድረኮች የአንበሳውን ድርሻ ይዘዋል። ገበያው እንዲሁ ዲጂታል ኢኮኖሚ የሚል መስመር የያዘ ነው። ደህንነትና ጦርነቱ በሳይበር ምህዳር ውስጥ የሚጠቃለል ነው። በግርድፉ ቴክኖሎጂና ሳይንሳዊ ውጤቶች የዘመናችን የኃያልነት ቁልፉን በመዳፋቸው ስር ማስገባት ችለዋል። በዚህ የፉክክር መድረክ ላይ ከፊት ለመሰለፍ ደግሞ ከጨዋታው መርህ ጋር መግባባትን ያሻል። በቅድሚያ ለቴክኖሎጂና መሰል ሳይንሳዊ ጉዳዮች በርን ክፍት ማድረግ ይጠይቃል።

ታላላቅ አገራት ይህን መስመር በሚገባ እየተከተሉት ነው። የኢንዱስትሪውን አብዮት ከጨረሱ ከፍለ ዘመን አስቆጠሩ። እድገታቸውን አልጋ ባልጋ ካደረጉ ታላላቅ ቴክኖሎጂና የፈጠራ ውጤቶች ጋር ወደፊት ብለው ግስጋሴያቸውን ቀጥለዋል። አሁን ወደ አራተኛው ትውልድ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተሸጋግረዋል። አዲሱን ትውልዳቸውን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርት ለማነፅ የተለያዩ ስልቶችን ይነድፋሉ።

በዚህ ረገድ ኢትዮ ቴሌኮም ኢትዮጵያ በሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ ለምታሳየው እመርታ ጉልህ ድርሻን እየወሰደ ይገኛል። የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ እየሠራ ያለው «ኢትዮ ቴሌኮም» ከዚህ አኳያ ሰፋፊ ሥራዎች እያከናወነ ይገኛል። ኩባንያው ባለፉት አስርት ዓመታት ፈጣን እድገት ማስመዝገብ ከቻሉ ታላላቅ የመንግሥት የልማት ተቋማት መካከል እንደሚመደብ መረጃዎች ያመለክታሉ። በተለይ ተደራሽነትና ጥራትን ግብ በማድረግ ሰፊው የማኅበረሰብ ክፍል የቴሌኮም አገልግሎቶችን እንዲያገኝ እየሠራ ነው።

በኢትዮጵያ 2ኛው የቴሌኮም አቅራቢ ድርጅት ሳፋሪኮም በቅርቡ ድርሻ ገዝቶ ሥራውን እስከ ጀመረበት ጊዜ ድረስም ሙሉ ለሙሉ የአገሪቱን ዜጎች የቴሌኮም አገልግሎት ፍላጎት ለማሟላት እየሠራ ቆይቷል። አሁንም ቢሆን ኩባንያው ትልቁን ድርሻ ይዞ የተለያዩ የቴሌኮም ዘርፍ አገልግሎቶችን እየሰጠ ይገኛል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በቴክኖሎጂ ዘርፍ ምርምሮችና ማስፋፊያዎችን በማድረግ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ማስተዋወቁንና ወደ ሥራ ማስገባቱን አጠናክሮ ቀጥሏል። ይህም የተጠቃሚውን ፍላጎት በተለያየ መንገድ ከመመለስ ባሻገር አቅሙን ለማጎልበትና ተወዳዳሪነቱን ከፍ ለማድረግ እንደሚረዳው ታምኖበታል።

ኢኮኖሚውንም ሆነ የእድገት ጉዞው በሳይንስና ቴክኖሎጂ የተመራ እንዲሆን በማገዝ እንዲሁም አዳዲስ መንገዶችን በማስተዋወቁ በኩል ተቋሙ ልዩ ልዩ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። በቅርቡ የኢትዮጵያ መንግሥት «ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025» ስትራቴጂን ለማሳካት ያዛሉ ባላቸው ሰፋፊ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ተሳትፎ እያደረገ ይገኛል። ከዚህ ውስጥ አዲሱ ትውልድ ከቴክኖሎጂና ፈጠራ ሥራዎች ጋር ያለውን ዝምድናና ቁርኝት እንዲያሳድግ ለማድረግ የልህቀት ማእከል በመሆን የእውቀት ሽግግርና ልማት ለማድረግም እየሠራ ነው።

ለተለያዩ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ስልጠናዎችን እየሰጠ ያለው ኩባንያው፣ በቅርቡ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በተመረቀው የሳይንስ ሙዚየምም የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና አገልግሎቶችን ይዞ በመቅረብ ለጎብኚዎች እያሳየ ይገኛል። በተለይ ሕፃናት እና ወጣት ጎብኚዎች በሳይንስ ሙዚየሙ ኢትዮቴሌኮም ባቀረበው ዓውደ-ርዕይ የዘመናችንን ድንቅ የቴክኖሎጂና የዲጂታል ግኝቶች በአይናቸው አይተው እና ሞክረው ለፈጠራ እና ምርምር መነሳሳት የፈጠረ ራዕይ እንዲሰንቁ እየሠራ ያለው ተግባር በምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል።

ዘመናዊ ክላውድ ላይ የተመሠረተ ሁሉን አቀፍ የግንኙነት ማእከል (Omni-channel Contact Center) ተግባራዊ ካደረገ ጥቂት ቀናት ነው የተቆጠሩት። በአገልግሎቱ ከዚህ ቀደም ደንበኞችን በድምፅና በተወሰኑ የሶሻል ሚዲያ አማራጮች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በተናጠል ያስተናግዱ የነበሩ የጥሪ ማዕከሎችን አሠራር ያዘመነና በልዩ ልዩ አማራጮች ማለትም በድምጽ፣ በአጭር የጽሑፍ መልዕክት፣ በኢሜል፣ በድረ-ገጽ፣ በማህበራዊ ሚዲያዎች፣ እንዲሁም ቻትቦትን (Chatbot) በመጠቀም የሚቀርቡ የደንበኞች ጥያቄዎችን በአንድ ላይ አቀናጅቶ ለደንበኞች አገልግሎት ባለሙያዎች በማቅረብ ቀልጣፋና ተደራሽ የደንበኞች አገልግሎት ማቅረብ የሚያስችል ቴክኖሎጂ ኩባንያው ይፋ አድርጎ ነበር።

ቴክኖሎጂው በአገር ውስጥ መጀመሩ ድርጅቶች እና ተቋማትም ይህን ተጠቅመው የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ለማሳለጥ ብሎም የደንበኞቻቸውን ተሞክሮ እና እርካታ በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ የሚችሉበት ትልቅ ዕድል መሆኑን የኢትዮ ቴሌኮም ሥራ አስፈፃሚ የሆኑት ወይዘሪት ፍሬህይወት ታምሩ ገልጸው ነበር።

የዝግጅት ክፍላችን በቅርቡ ተመርቆ ለሕዝብ አገልግሎት ይፋ የሆነው የሳይንስ ሙዚየም ተገኝቶ ምልከታ ባደረገበት ወቅትም ኢትዮ ቴሌኮም የተገበራቸውን የቴክኖሎጂ አማራጮች ለእይታ ቀርበው ጎብኝቷል፤ ከዚህ ባሻገር ደግሞ ሕፃናትና ወጣቶች የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በአካል በማየትም ሆነ ልምምዶችን በማድረግ ከህልማቸው ጋር እንዲቀርቡና ቀጥተኛ ትምህርት እንዲያገኙ የሚያስችሉ ተግባራትን ሲያከናውኑ ለመመልከት ችሏል።

እየሩሳሌም ባዬ ትባላለች። እሷ የምትሠራበት ኢትዮ ቴሌኮም በሙዚየሙ ውስጥ ለታዳጊዎች የሚሰጠውን የሮቦት ደረጃ አንድ ስልጠና እየሰጠች እያለች አገኘናት። እርሷ እንደምትለው፣ ኩባንያው ተፈታትኖ አገር ውስጥ የገቡ ሮቦቶችን ታዳጊዎች መገጣጠምና አገልግሎት ላይ እንዲያውሉ ማድረግ እንዲችሉ በሙዚየሙ ውስጥ ስልጠና ይሰጣል። ይህም ታዳጊዎቹ ከቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ጋር የበለጠ ቁርኝት እንዲኖራቸውና ለወደፊት የመፍጠር አቅማቸው እንዲጎለብት እንደሚረዳቸው ትናገራለች።

እየሩሳሌም እንዳለችው፣ የዚህ ሁሉ አላማ ሕፃናትና ታዳጊዎችን በቴክኖሎጂ የበለፀገች አገር ተረካቢና መሪ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፤ ኢትዮ ቴሌኮም በሙዚየሙ ውስጥ የዱሮዎቹን፣ የአሁኖቹንና ወደፊት እንደሚመጡ የሚጠበቁትን የቴክኖሎጂ ውጤቶች ይዞ በመቅረብ እያስተዋወቀ ይገኛል። በዚህም ለማህበረሰቡም ሆነ ለኢትዮጵያ መንግሥት ታዳጊዎች ላይ ከስር መሠረቱ ጀምሮ የቴክኖሎጂ ፅንሰ ሃሳብ እንዲጎለብት መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

እየሩሳሌም ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ የሂሳብ (ማቲማቲክስ) ትምህርት ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት ለአገር እድገት ወሳኝ ነው ትላለች። በሌላ በኩል ኢትዮ ቴሌኮም ሮቦቶች የ5ጂ ኔትወርክን ተጠቅመው የሰው ልጆች በሚሠሩበት ፍጥነት ፕሮግራም የተደረጉበትን ተግባራት እንዲያከናውኑ ለማስቻል ትልቅ እገዛ እንደሚያደርግ ጠቅሳ፣ በዚህ ዘርፍ ላይ ወጣቶችም ሆኑ ታዳጊዎች ተሳትፈው እውቀት ቢጨብጡ በቀጣይ ጊዜያት አገሪቱ ውጤታማ ለማድረግ በሚከናወኑ ተግባሮች ቁልፍ ድርሻ እንደሚኖራቸው ትጠቁማለች። ለዚህ መሰል ውጤታማ ሥራ ደግሞ ኩባንያው ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን ነው ያስታወቀችው።

«በቀጣይም አገራችን ይህን መሰል የሳይንስ ሙዚየሞች አገራችን ያስፈልጋታል። ይህ እውን በመሆኑም ደስተኛ ነኝ» የምትለው እየሩሳሌም፣ ኢትዮጵያ እውን ልታደርገው ለቀረፀችው ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ኢትዮ ቴሌኮም ቁልፍ አጋርና የፊት መስመር ተሰላፊ ነው ትላለች። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነውም በሙዚየሙ ውስጥና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ጉልህ ድርሻና ኃላፊነትን ወስዶ እያከናወነ ያለው ተግባር መሆኑን ጠቅሳለች። እየሩሳሌም ኢትዮጵያን ዲጂታላይዝ የማድረጉ ግብም እንደሚሳካ እምነቷ ነው።

ታዳጊ ስምኦን የሐንስን ኢትዮ ቴሌኮም በሳይንስ ሙዚየም ውስጥ እየሰጠ በነበረው የደረጃ አንድ ሮቦት ፕሮግራሚንግ ስልጠና ላይ ያገኘነው። እርሱ እንደሚለው፣ በራሱ ፍላጎት የቀረቡለትን ሮቦቶች በፍጥነት በማስተካከል፣ ቀለማቸውን በመምረጥ እንዲሁም የራሱን መረጃዎች በሚፈልገው መንገድ ፕሮግራም በማድረግ የተለያዩ ልምምዶችን ማድረግ ችሏል። በዚህ ሙዚየም ውስጥ በመገኘቱ እጅግ ደስተኛ እንደሆነ የሚገልፀው ስምኦን ወደፊት በተለያዩ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችና በሮቦት ፕሮግራሚንግ ላይ አዳዲስ ነገሮችን መሥራት እንደሚሻ ይገልፃል። በስልጠናው እውቀት ከማግኘቱም በላይ ወደ ትምህርት ቤቱ ሲመለስ ጓደኞቹም ይህን ስልጠና እንዲወስዱ እንደሚያበረታታቸው ነግሮናል።

ሌላኛው ታዳጊ ደግሞ ስምን ታለ ነው። እርሱም በኢትዮ ቴሌኮም የሮቦት ስልጠና ላይ ነበር ያገኘነው። በተለይ ተፈታትቶ የተሰጠውን ሮቦት በምን መልኩ መልሶ መገጣጠምና እርሱ በሚፈልገው መልኩ መጠቀም እንደሚችል ከተማረ በኋላ በተግባር ሊሠራው ችሏል።

«በዚህ የሳይንስ ሙዚየም በመገኘቴ ተደስቻለሁ። ከዚህ ቀደም እንደዚህ ዓይነት ዘመናዊ ቴክኖሎጂና ስልጠናዎችን አይቼም ሆነ ሰልጥኜ አላውቅም ነበር» የሚለው ታዳጊ ስምን ታለ፣ አሁን ግን ህልሙን የሚያሳካና እንዲበረታታ የሚያደርገው ዕድል እንዳጋጠመው ይናገራል። ወደፊት ታዋቂ አገር ኣስ ተጨዋች ለመሆን እንደሚፈልግ ጠቅሶ፣ በቴክኖሎጂና ሳይንሳዊ ምርምሮች ላይ ውጤታማ ሥራዎች የመስራት ህልምም እንዳለውም ገልጧል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሙዚየሙን መርቀው በከፈቱበት ወቅት እንዳሉት፣ የሳይንስ ሙዚየሙ በሳይንስ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ዘርፍ ተወዳዳሪ ዜጋ ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት በማገዝ ዓይነተኛ ሚና ይጫወታል። በአገራችን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወጣት ቢኖርም ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ዘርፍ የተመቻቸ ቦታ ባለመኖሩ የወጣቶችን እምቅ የፈጠራ አቅም መጠቀም ሳይቻል ቆይቷል።

እንዲህ ያለ የሳይንስ ሙዚየም መኖሩ ወጣቶች ተሰጧቸውን አውጥተው ለመጠቀም ዕድል የሚፈጥርላቸው መሆኑንም ጠቅሰው፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የተነቃቃ አዲስ ትውልድ ለመቅረጽም ዓይነኛ ሚና እንደሚኖረው አስረድተዋል።

ሳይንስና ጥበብን በሁለት አተያይ ያጣመረው ሙዚየሙ፣ በአገር ውስጥ ያሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለእይታ የሚቀርቡበትና የሚተዋወቁበት፣ ምርምር የሚደረግበት፣ የምርምር ሥራዎች የሚቀርቡበት እና ወጣቶች ንድፍ ሃሳባቸውን ወደ ተግባር የሚቀይሩበት እንደሆነም አመልክተዋል። ወጣቶች እንዲጎበኙትም ጥሪ አቅርበው ነበር።

ሙዚየሙ ከተመረቀ አንስቶም በተለይ በሳምንቱ መጨረሻ ቀናት እጅግ በርካታ ወጣቶች ታዳጊዎች እና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች እየጎበኙት ይገኛሉ። የትናንት የኤፒድ ዘገባ እንዳመለከተው ፣ የሳይንስ ሙዚየም የጉብኝት ጊዜ ለአንድ ወር መራዘሙን ኢትዮ ቴሌኮም አስታውቋል። የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሪት ፍሬህይወት ታምሩ ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደገለፁት፣ የሳይንስ ሙዚየሙን ለመጎብኘት ባለው ሰፊ ፍላጎት ምክንያት የመጎብኛ ጊዜውን መጨመር አስፈልጓል።

እንደ ወይዘሪት ፍሬህይወት ገለፃ፣ የሳይንስ ሙዚየሙ በ19 ቀናት ውስጥ 357ሺህ ጎብኚዎች የጎበኙት ሲሆን፣ ባሳለፍነው ቅዳሜና እሁድ ብቻ ከ109ሺህ በላይ ሰዎች ጎብኝተውታል።

ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ ሙዚየሙን ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉ ዜጎች እንዲጎበኙት ለማድረግ የሚያስችል ሥራ እየተከናወነ መሆኑንም አስረድተዋል። ሙዚየሙ ትናንት (ጥቅምት 13 ቀን 2015 ዓ.ም) ብቻ ከ75 ሺህ በላይ ጎብኚዎችን አስተናግዷል ብለዋል።

የፈጠራ ሥራዎቻቸውን፣ አገልግሎቶቻቸውን ይዘው የቀረቡት ኩባንያዎች እና ድርጅቶችም በርካታ ናቸው። በቦታው የተገኘነም የሚጠይቁት እየጠየቁ፣ የሚያስረዱት እያስረዱ፣ የሚያዳምጡት እያዳመጡ፣ የሚመለከቱት እየተመለከቱ ፣ ቴክኖሎጂዎችን የሚፈትሹና የሚገጥሙትም ሲፈቱና ሲገጥሙ እኛም ተመልክተናል። ሙዚየሙ ለወጣቶችና ታዳጊዎች ብቻ ሳይሆን ለመላ ተማሪዎችና ምሁራንም የተበረከተ ትልቅ የምርምር ማእከልና ስጦታ ነው ማለት ይቻላል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ኢትዮ ቴሌኮም ወሳኝ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# እየናረ የመጣውን ጥቁር ገበያ ለመቆጣጠር - ዘላቂ መፍትሔ

**አስመረት ብስራት**

በወቅታዊ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እየናረ የመጣውን የጥቁር ገበያ ለመቆጣጠር ሲባል ከውጭ ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ክልከላ ለተደረገባቸው 38 የምርት ዓይነቶች ባንኮች ከጥቅምት 7 ቀን 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ኤል.ሲ (ሌተር ኦፍ ክሬዲት) መክፈት እንደማይችሉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መግለጹ ይታወቃል።

ተሽከርካሪን ጨምሮ 38 ምርቶች እንዳይገቡ በመወሰኑ፣ ባንኮችም በዚህ ውሳኔ መሠረት ለምርቶቹ የውጭ ምንዛሪ እንዳይፈቅዱ መመሪያ እንዲደርሳቸው መደረጉ ከሰሞኑን ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው። ከተሽከርካሪዎች ሌላ ክልከላ ከተደረገባቸው ምርቶች ውስጥ እንደ ከረሜላ፣ ማስቲካና ጣፋጭ ምግቦች ተጠቃሽ ናቸው። የተለያዩ የፍራፍሬ ጭማቂዎች፣ ሲጋራ፣ ውስኪ፣ ወይንና ሌሎች የአልኮል መጠጦች በዚህ መመሪያ መሠረት ላልተወሰነ ጊዜ እገዳ የተጣለባቸው ናቸው።

የባንኩ ምክትል ገዥና ቺፍ ኢኮኖሚስት አቶ ፈቃዱ ደግፌ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ለእነዚህ ምርቶች ማንኛውም ባንክ ኤል.ሲ መክፈት አይችልም። ይህንን መመሪያ ጥሰው ኤል.ሲ የሚከፍቱ ባንኮች ካሉ ሕግ በመተላለፍ ተጠያቂ የሚሆኑና የሚቀጡ ይሆናል።

የውጭ ምንዛሪ የማይፈቀድላቸው 38 የምርት ዓይነቶች መከልከላቸው ፋይዳው ምን እንደሆነና በጥቁር ገበያ የሚዘረዘረው ዶላርም ከ100 ብር በላይ ደርሶ የነበረ ቢሆንም፤ ከዕርምጃው በኋላ ከ70 ብር በታች የመሆኑ ምስጢር በተደረገው ውሳኔ የመጣ ለውጥ ነውን? ስንል በጉዳዩ ዙሪያ የዘርፉን ባለሙያዎች አነጋግረናል።

የፓን አፍሪካ የንግድ እና የኢንዱስትሪ ምክር ቤት ዋና ዳይሬክተር አቶ ክቡር ገና እንደሚናገሩት፤ በተወሰኑ ምርቶች ላይ የተጣለው የውጭ ምንዛሪ እገዳ እየጨመረ ያለውን የዋጋ ንረት ያረጋጋል። ተተኪ ምርቶች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ ምክንያትም ይሆናል።

ብሔራዊ ባንክ 38 ምርቶች ላይ ላልተወሰነ ጊዜ የውጭ ምንዛሪ እገዳ መጣሉን ተከትሎ አገር ውስጥ ያሉ የፋብሪካ ባለቤቶች አስፈላጊ ናቸው ብለው የገመቱትን በአገር ውስጥ ለማምረት የሚሞክሩበት አንድ ምክንያት ሊሆን ይችላል ነው ያሉት። እንደእርሳቸው አባባል፤ ድጋፍ ከተሰጠ እና እገዛ ከተደረገ የአገር ውስጥ አምራቹን በማነሳሳት ከውጭ ይገቡ የነበሩና የታገዱ ምርቶች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ የሚያደርግ ጥሩ ምክንያት ይሆናል። የቅንጦት እቃዎች ዋጋ በየጊዜው የአገሪቱ የዋጋ ግሽበት ላይ ተጽእኖ እያሳደረ በመሆኑ ለእቃዎች ግዢ ይውል የነበረው ገንዘብ ለልማት እና እሴት ጨምረው ለሚወጡ ዕቃዎች የሚውል በመሆኑ ይበል የሚያሰኝ ተግባር ነው።

እገዳ እንዲጣልባቸው ከተዘረዘሩት ሚዛን የሚደፉት ተሽከርካሪ እና ከተሽከርካሪ ጋር የተያያዙት ናቸው ያሉት ባለሙያ፣ እነዚህ ቀርተው ገንዘቡን ለመሠረታዊ የፍጆታ እቃዎች እና ለልማት እንዲውል ማድረጉ ጥሩ እርምጃ ነው ብለዋል። ብሔራዊ ባንክ ከውጭ ይገቡ በነበሩ ምርቶች ላይ የጣለው እገዳ አገሪቱ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ብትሆንም ብዙም አስቸጋሪ ነገር አይፈጠርም ብለዋል።

ብሔራዊ ባንክ ጥቁር ገበያውን ፈቅዶ አያውቅም፤ አሁንም የተወሰዱትን እርምጃዎች አጠናክሮ መቀጠል ተገቢ ነው። ድርጊቱን የሚፈጽሙት ሕገ ወጦች የማስቆም ጅማሮ መልካም ሲሆን፣ አሁንም መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት መስጠቱ እጅግ የሚደገፍ ሀሳብ ነው። ውሳኔውን ተከትሎም በጥቁር ገበያ በሚደረገው ግብይት የአንድ ዶላር ዋጋ ከ100 ብር በላይ ደርሶ የነበረውን በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት በማስተካከል ፖሊሲው ውጤት እያመጣ መሆኑን ያሳያል ሲሉ ባለሙያው ይናገራሉ።

ይሁንና ይህ እስከመቼ ይቀጥላል ለሚለው በሰጡት ምላሽ፤ «ገና አልታወቀም» የሚል ምላሽ ያስቀምጣሉ። እንዲያም ሆኖ የመጀመሪያዎቹ ምልክቶች ግን የተፈለገውን ዓላማ ለማሳካት እንደሚያስችል አሳይቷል ብለዋል። በቂ ምርቶች በብቃት አለመግባታቸው ወይም አለመመረታቸው ግሽበትን እንዲፈጠር አድርጓል። በሰዎች እጅ ብዙ ገንዘብ አለ፤ ነገር ግን ሰው የሚፈልገውን የሚያገኝበት ሁኔታ አለመፈጠሩም አሳሳቢ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

በአጠቃላይ ሲታይ ትልቁ ግሽበት እየመጣ ያለው በምግብ በመሆኑ በተለይ አቅመ ደካማውን የሚጎዳ ነው። ከተማ ውስጥ የሚታየው የቤት ኪራይና ሽያጭ ላይ የሚስተዋለው ዋጋ ከዕለት ወደ ዕለት እየናረ ሄዷል። አንዳንድ አገራት ከተወሰነ ገንዘብ በላይ የሚያወጣ ሽያጭ ካለ ታክሱ በጣም ከፍተኛ ይሆናል። በእኛ አገርም መጠናት ይኖርበታል ብለዋል።

አሁን የተወሰደው እርምጃ በተወሰነ መልኩ የውጭ ምንዛሪ ቢያድንም ምን ያህል? የሚለው ጥያቄ ውስጥ ሊገባ ይገባዋል። ምክንያቱም እገዳ የተጣለባቸው ከአውቶሞቢል ውጪ ሌላው ቢተመን በዓመት ውስጥ ከ100 ሚሊዮን ዶላር በታች እንጂ ከእዛ በላይ አያወጣም። በርግጥ ይሄ ቀላል ነው ማለት ባይሆንም ሚዛን ደፊ አይደለም ብለዋል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዛፉ እየሱስ ወርቅ ዛፉ እንደሚሉት፤ የጦርነት ኢኮኖሚ ውስጥ የሚገኘውን የአገሪቱን ወቅታዊ ሁኔታ ለመታደግ ብሔራዊ ባንክ እየወሰደ ያለው እርምጃ መልካም ነው። በመንግሥት በኩል የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት፤ ያለምንም የውጭ ምንዛሬ ፍቃድ (ፍራንኮ ቫሉታ) በጉምሩክ በኩል በቀጥታ እንዲገቡ የተፈቀደውን ውሳኔ ያለአግባብ ጥቅም ላይ የሚያውሉ አካላት የሚያደርጉት ተግባር ተገቢ አይደለም።

እርሳቸውም እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ የማክሮ ኢኮኖሚ ፈተናዎች ገጥሟታል። ይህንን ችግር በመገንዘብ መንግሥት እየሠራበት ይገኛል፤ ሆኖም ለመፍትሄው የተጀመሩ ጥረቶች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል። በአገሪቱ ለሚስተዋለው የኢኮኖሚ ችግር ኃላፊነቱን የመንግሥት ብቻ አድርጎ መመልከት ትልቅ ስህተት ነው። መንግሥት፤ ድርጅቶች በአንጻራዊ ሰላም ሁኔታ ሥራቸውን እንዲሠሩ ማድረግ ይገባል። የኑሮ ውድነቱ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉና አነስተኛ ገቢ ያላቸውን በከፍተኛ ደረጃ ቢያጠቃም፣ የመንግሥትና የግል ዘርፉ ሠራተኞችንም ስለሚጎዳ ለመንግሥት ብቻ ሊተው አይገባም።

አቅርቦትን ከፍ ማድረግ በአንድ ሌሊት የሚሆን ጉዳይ አይደለም ያሉት አቶ ዛፉ ኢየሱስወርቅ፣ ጉዳዩ ጊዜ የሚፈጅ፣ ሂደትን አልፎ የሚዘጋጅ ነው ብለዋል። መንግሥት የውጭ በጀቱን ያህል የውስጥ ገቢን ሊሰበስብ ይገባል። በአገር ውስጥ የውጭ ምንዛሬ አቅም ላይ የሚስተዋለውን መመናመን ማስተካከል እንደሚገባውም ይጠቁማሉ።

በሕገወጥ መንገድ የሚካሄዱ የውጭ አገር ምንዛሬ እና ክምችትን፣ የወርቅ ዝውውርና ክምችት፣ የሐሰተኛ የብር ኖቶች ሕትመትን ለመቆጣጠር ሕገወጥ ድርጊቶችን ለመጠቀም ብሔራዊ ባንክ ማበረታቻ አስቀምጧል። ፍራንኮ ቫሉታን በሕገ ወጥ መንገድ ተግባር ላይ በሚያውሉ ግለሰቦች ላይም ማበጀት ይገባል ያሉት አቶ ዛፉ፣ ለሰላም መስፈን ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባዋልም ብለዋል።

እንደ እርሳው ገለጻ፤ ኢትዮጵያ የማክሮ ኢኮኖሚ ፈተናዎች ገጥሟታል። ይህንን ችግር በመገንዘብ መንግሥት እየሠራበት ይገኛል፤ ሆኖም ለመፍትሄው የተጀመሩ ጥረቶች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያ አቶ ወሰን ሰገድ አሰፋ በበኩላቸው፤ አገሪቱ ከሚያስፈልጋት ነገር አንፃር ሲታይ ይታገዱ በተባሉት 38 ምርቶች የምናጣው ዶላር በጣም ብዙ አይሆንም። ይህ ማለት አገር ውስጥ እንዳይገቡ የተከለከሉት ምርቶች ያን ያህል አስፈላጊ የሚባሉ ባለመሆናቸው መሠረታዊ ያልሆኑትን ነጥሎ ማስቀረቱ መልካም ተግባር ሊባል የሚችል ነው። ያን ያህል መሠረታዊ ያልሆኑ የማህበረሰቡ ሕይወት ላይ ይህ ነው የሚባል ለውጥ የማያመጡ መሆናቸው ይበል የሚሰኝ ተግባር ሆኖ ሳለ ለዶላር እጥረቱ መፍትሄ ነው።

የቁሳቁስ ከውጪ እንዳይገባ ክልከላ ሲደረግ ቀድመው በአገር ውስጥ ገብተው የነበሩ አሁን ላይ የተከለከሉ ቁሶች የመሸሸግ እጣም ሆነ ዋጋቸው ከፍተኛ መሆኑ አይቀርም። በቀጣይ ወራት ምርቶቹ ወደ ጥቁር ገበያ እና ኮንትሮባንድ ሥርዓት ውስጥ ሊገቡ የሚችሉበትን ሁኔታም ሊፈጥሩ የሚችሉ መሆኑን ጠቁመዋል።

የክልከላው ዓላማም ምርቱን ከአገር ውስጥ ገበያ በተዘዋዋሪ ማጥፋት ስለሆነ በአጭር ወራት ገበያው ከሸቀጦች ዝርዝር በውዴታ ሳይሆን በግዴታ የተከለከሉ ቁሶችን ጭራሽ ባይሆንም በብዛት ስለሚያስወጣቸው ቅፅበታዊ የዋጋ መጨመሮች በሂደት መስተካከላቸው አይቀርም ብዬ አስባለሁ ብለዋል።

የዶላር እጥረቱን ለመቆጣጠር ዶላር ከሚያሳጡን ነገሮች ይልቅ ዶላር የምናገኝባቸው ነገሮች ላይ ማተኮር ይበልጥ አገሪቱ ከገባችበት ቀውስ እንድትወጣ ደጋፊ መፍትሄ ሀሳብ መወሰድ አለበት ይላሉ።

ይህንን ለማግኘት ደግሞ በኤክስፖርት አቅምን ማሳደግ፤ የቱሪዝም ሀብትን ለጎብኚዎች ክፍት ከማድረግና ቱሪስቶች ወደ አገር ውስጥ የሚገቡበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤ ከውጭ የሚላኩ ገንዘቦች በሕጋዊ መንገድ እንዲሆን በማደረግ የውጭ ምንዛሪ ክምችትን መጨመር ዘላቂ መፍትሄ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ መንግሥት እዚህ ላይ ትኩረት ሊያደረግ ይገባል ሲሉም ተናግረዋል።

ሌላው ሕዝቡ በመንግሥት ላይ አመኔታ እንዲኖረው ማድረግ ሕጋዊ መንገዶችን ዜጎች እንዲጠቀሙ ሊያደርግ ይችላል። ይህ ሲባል የጥቁር ገበያና የሕጋዊ ገበያውን ልዩነት ማጥበብ፤ ለቤተሰቦች የሚላከው ገንዘብ በብር ሲለወጥ ከሚያስፈልገን ዶላር አንፃር በመመልከት ምንዛሪውን መጨመር፤ ዲያስፖራው ማህበረሰብ አገሩ ውስጥ ያለውን ልማት እንዲደግፍ ተአማኒነት ያለው አሠራር መዘርጋት ከሙስና የፀዳች አገር መኖሯን የሚያሳይ ተግባር ሲከናወን ውጭ አገር ያሉ ዜጎቻችን ገንዘብ የማይልኩበት ምክንያት አይኖርም በማለትም ገልጸዋል።

አቶ ክቡር ገና በበኩላቸው፤ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ ድርጅቶች ካሉ ግብዓቶችን በቀላሉ እንዲያገኙ። የገንዘብም ሆነ የብድር ድጋፍ ቢመቻች በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርቱን አሳድገው የገበያውን ዋጋ ሊያስተካክሉት ይችላሉ። በዋናነት ግን በተለይ የግብርና ምርትን ማሳደግ ላይ ብዙ ሊሠራ ይገባል። በአገር ውስጥ ያለው ሀብት መሬት እንደመሆኑ ምርትን ማሳደግ በሚቻልበት መንገድ ጥቅም ላይ በማዋል መሠረታዊ ችግሩን መፍታት ያስፈልጋል።

ሌላው የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ በመቀየርና ቁጥጥሩን አጠናክሮ በመቀጠል ለውጥ ማምጣት ይቻላል የሚሉት የኢኮኖሚ ባለሙያው፣ ጦርነቱን በማስቆም የቱሪዝም ሀብቱን ለመጠቀም የሚያስችል ቅድመ ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ነው በማለት አስረድተዋል። ይህ ሲባል አገሪቱ የሚኖራትን የዶላር ሀብት ለመጨመር የሚያስችሉ መፍትሄዎችን መመልከትም ሌላው አማራጭ መሆኑን አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊው ባንክ የውጭ ምንዛሪ ዝውውርን በተመለከተ ገደብ እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪዎችን ተግባራዊ ሲያደርግ ይህ የመጀመሪያ አለመሆኑ ይታወሳል። የኢትዮጵያ ባንኮች በተለያዩ መንገዶች እጃቸው ከሚገባው የውጭ ምንዛሪ 70 በመቶውን ወደ ማዕከላዊ ባንክ እንዲያስተላልፉ ጥር 2 ቀን 2014 ዓ.ም በባንኩ ገዥ ፊርማ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ተግባራዊ እንዲሆን መደረጉ ይታወሳል።

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ፈንድ (IMF) በዘንድሮ ትንበያው የቀጣይ ዓመት የኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ ክምችት የሽመታ አቅም አሁን ካለበት 21 ቀን ወደ 18 ቀን ዝቅ ሊል ይችላል ብሏል። በ2014 ኢትዮጵያ ከውጪ የሚያስፈልጋትን ቁሳቁስ በተወሰነ መልኩም ለመሸመት ከ18 ቢሊዮን ዶላር በላይ እንዳወጣች ይታወቃል። ስለዚህ በ2022 በግርድፉ ከተሰላ 1 ነጥብ 03 ቢሊዮን ዶላር ገደማ የውጭ ምንዛሬ ክምችት በካዝናዋ አላት እንደማለት ነው ሲል አመልክቷል።

ለዚህ መፍትሄው ምሁራኑ እንዳመላከቱት ከክልከላው ይልቅ የውጭ ምንዛሪ የሚገኝበትን አማራጭ በስፋት መመልከት እንዲሁም የቁጥጥር ዘዴውን ማጠናከር፤ እንዲሁም ተኪ ምርቶችን በብዛት ማምረት ነው።

**አንዳንድ ቁሳቁስ ከውጭ እንዳይገባ ክልከላ ሲደረግ ቀድመው በአገር ውስጥ ገብተው የነበሩትን የተከለከሉ ቁሶች የመሸሸግ እጣም ሆነ ዋጋቸው ከፍተኛ መሆኑ አይቀርም። በቀጣይ ወራት ምርቶቹ ወደ ጥቁር ገበያ እና ኮንትሮባንድ ሥርዓት ውስጥ ሲገቡ የሚችሉበትን ሁኔታም ይፈጠራል**

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ከቀንድ ዋንጫው በስተጀርባ

ጽጌረዳ ጫንያለው

ስለ «ጠላ ቤት» ሲነሳ በአብዛኞቻችን አዕምሮ ውስጥ ቀድሞ የሚመጣው የሴቶች ልፋትና ውጣውረድ ሊሆን ይችላል። አለፍ ስንል ደግሞ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚተዳደሩበት የሥራ መስክ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸውን መጠጦች መጠጣት የማይችሉ ሌሎች ደግሞ የሚዝናኑበት እንደሆነ እናስባለን። ሥራውን በጎ ካልሆኑ ገጽታዎቹ ጋር ብቻ የምናስብም አንጠፋም። ለምን ከተባለ በዚህ ስፍራ ሁልጊዜ ስካርና ሁካታ ስላለ ነው። ከዚሁ ስሜት ጋር ተያይዞ ክፉ ቃላቶች ይወጣሉ፤ ጉንተላና ስድብ፣ ከዚህም አልፎ ድብደባና ደም መፋሰስ አይጠፋም። እናም ከኮማሪቷ ድካምና ልፋት በላይ ትዝ የሚለን በቦታው የሚያጋጥሙት ነገሮች ናቸው።

በአብዛኞቻችን ዘንድ አንዲት ጠላ ነጋዴ ይህንን ሥራ ለምን እንደመረጠች የሚረዳ የለም። ኑሮን ለማሸነፍ ዝቅ እንዳለች ከመገንዘብ ይልቅ የበታችነቷን ተቀብላ እንድትኖር ብቻ ይፈርዱባታል። በቻሉት ልክም ጫናውን ያሸክሟታል። አንዳንድ ደንበኞቿ ደግሞ የስድብ ናዳ ያወርዱባታል፤ ያዋርዷታል፣ ባስ ካለም ቡጢ ጡጫውን ያቀምሷታል። እንዲህ ዓይነቶቹን ማንነቶች እንድትለምደው፤ ኀዘናቸውን፣ ንዴታቸውን ባህሪያቸውን ጨምሮ ሁሉን እንድትቋቋመው ይፈረድባታል። አልፈው ተርፈውም ጾታዊ ትንኮሳ ያደርሱባታል።

ሰዎቹ የቀን ገቢ ያላቸው ለፍቶ አዳሪዎች ቢሆኑም እንኳን ታታሪዋን ሴት በብዙ መልኩ ይፈትኗታል። እንዲህ መሆኑ ደግሞ ጠላ ቤቱ በብዙ ጎዶሎዎች መሀል ከጨዋነት መስመር ስቶ እንዲወጣ ያደርገዋል። በአብዛኞቹ ጠላቤቶች እስካሁን የለመድነውና እያስተወልነው የመጣነው እንዲህ ዓይነቱን እውነት ነው።

በጠላ ቤቱ ጎራ የሚሉ አንዳንድ ደንበኞች ውሃ በጠማቸው ጊዜ ለጉሮሯቸው ማርጠቢያ ጠላዋን ተጎንጭተው በዚያው ልክ ስድብና ጡጫቸውን አሳርፈው የሴቷን ሕመም አብዝተው ይወጣሉ። በጠላ ሽያጩ ላይ የምትቆመው ሴት ግን መቼም ቢሆን አምርራ መቀየም አይቻላትም። ምክንያቱም በበዛ ጥረትና ድካም የምትደፍነው ጉሮሮ ይጠብቃታልና። በተለይ ትዳሯን የፈታችና ባሏ የሞተባት ሴት ልጆቿንና ራሷን ለማሳደር ይህ ዓይነቱ ሥራ ዋነኛ አማራጭ ታደርጋለች። በውሎ አጋጣሚዋም የሁሉንም አመል ማረቅና መሸከም ከውዴታ ግዴታዋ ሆኖ አብሯት ይዘልቃል።

ብዙ ጊዜ ሴት ልጅ ሥራ ከበደኝ፣ አቃተኝ እንደማትል ከዕለት ተዕለት አድካሚ ሥራዎቿ መረዳት ይቻላል። እንዲህ ዓይነቷ ባለሙያ በዚህ ሥራ ብዙ ትለፋለች። ጌሾ መውቀጥ፣ ብቅል ማዘጋጀት፣ የጠላ ቂጣ መጋገር የእርሷ ሥራ ነው። ወፍጮ ፍጩልኝ ሳትል፤ ለጌሾ ወቀጣው ወንዶችን ሳትጠራ ሁሉንም በራሷ ታደርገዋለች።

በዚህ ልፋት ድካሟ መሀልም የዚህችን ሴት በረከት የሚሹ ነፍሶች ይጠብቋታል። እሷም ብትሆን ግዴታዋን ሁሉ ትወጣለች። ልጆቿን አሳድጋ ለወግ ማዕረግ ታበቃለች። ተግባሯ በልፋቷ ተሞሽሮ ከማሰሮው ማንቆርቆሪያ ይወርዳል። የቀንድ ዋንጫውን ሞልቶም በመዓዛው እያወደ በጣዕሙ ጥፍጥና ለሌሎች እርካታ ይደርሳል።

ይች ሴት ለድካሟ የማይመጥን ገንዘብ ለቅማ የሌሎችን ደስታ ሞልታ ልጆቿን ካሰበችው ስታደርስ፤ ከብርጭቆው በስተጀርባ ያኖረችውን ውጤት ታገኘዋለች። የብርታቷን ፍሬ ቀምሳ ታጣጥማለች።

የብርታቷን ፍሬ ከሚቀምሱት መካከልም ዛሬ የመረጥናት ብርቱዋ ሴት ወይዘሮ ዝናሽ አየለ አንዷ ናት። ታሪኳ እንደተለመደው ጠላቤት ኮማሪዎች ሳይሆን በራሱ መስመር የተጓዘና ለስኬት ያበቃት ነው። ይህንን ንግድ መተዳደሪያቸው ያደረጉ ሴቶች ዓይነትም አይደለችም። ንግዱን የጀመረችው ለአዕምሮዋ እረፍት ለባህሏ ክብር ለመስጠት ነው። ከዚያም አልፋ የሴቶችን ብርታት ለማሳየት ነው።

እነሱ መከሳት መጥቆራቸውን በፈገግታቸው፤ ጨለማ ችግራቸውን እንደ ሻማ ብርሃን ሆነው የልጆቻቸውን ቀን እንዳንቦገቦጉ ለማሳየት ተግታ



ትሠራለች። ብቸኝነታቸውን ከራሳቸው አዋህደው ዓመታትን ቢያሳልፉም ልጆቻቸውን ካሰቡት ላይ እንደሚያደርሱም ሆና ታሳያለች።

ጠላ ከልፋቱ ባሻገር ሌሎች ዓይን ገላጭ ነገሮችም እንዳሉት ምስክር ሆናለች። እንዴት ከተባለ ልፋቱን ከመቀነስና ከቦታው እንዲሁም ከጠጪዎቹ አንጻር በሠራችው ሥራ በማስደመም ነው። ሥራዋን አሀዱ ያለችው በከተማ በመሆኑ የጠላ አዘገጃጀቱ እንደገጠሩ ቢሆንም ልፋቱን ግን በብዙ መልኩ ቀንሳዋለች። በአብዛኛው ለጌሾ ወቀጣና ለብቅል መፍጨቱ ዘመናዊ ወፍጮ ቤትን ስለምትጠቀም ለእሱ የሚወጣውን ጉልበት ወደሌላኛው ሥራ ላይ እንዲያርፍ ታደርጋለች።

ጠላ በማኅበረሰቡ አሉታዊ ምልከታ የተነሳ ከጊዜ ወደጊዜ የነገሥታት መጠጥ ሳይሆን የድሆች እየሆነ በመምጣቱ በተለይ በአዲሱ ትውልድ ቦታ የሚሰጠው እንዳልሆነ ልብ ይሏል፤ ነገር ግን ይህች ልባም ሴት ጠንካራ በመሥራቷና በማሠራቷ አሁን ላይ በከተማው ሰው ዘንድ ሀሳቡ ተቀይሯል።

በቅጽል ስሟ «ደሸሾ» እየተባለች የምትጠራውና ጠላ ቤቷን በዚህ ስም ያደረገችው ዝናሽ፤ ከእናቷ በወሰደችው የጠላ ጠመቃ ሙያ እንዲሁም ቤተሰቧ ላይ በምታየው የባህል መጠጦች ፍቅር የተነሳ ሥራውን ስለመጀመሯ ትናገራለች። እንደ ገጠር ሴትነቷ በጠላ ጠመቃ ዙሪያ ያለውን ልፋት ባታውቀውም ክብር ያለው መጠጥ መሆኑን ግን ከቤተሰቦቿ ጋር በኖረችበት ዕድሜ ሁሉ አይታለች። በእነርሱ ቤት በርካቶች እንደሚያደርጉት ለበዓላትና ለሌሎች ድግሶች ባህላዊ መጠጦች ይዘጋጃሉ፤ በቤቱ ጠላ ጠፍቶ አያውቅም። ፍቅርን፣ መተሳሰብን፣ መሰባሰብን፣ ለችግር መፍትሄን መፈለግን ለማምጣት ጠላ ትልቅ ድርሻ አለው። ስለዚህ ልዩ ክብር ሰጥታ እንድትሠራበት ብትሆንም መተዳደሪያዬ ይሆናል ብላ አላሰበችም ነበር። ነገር ግን ከሚሰጣት አስተያየትና ሙገሳ አንጻር ሥራውን ወዳና የተሻለ አድርጋ በመሥራቷ ዛሬ ላይ የገቢ ምንጯ ሆኗል።

## ትንሿ ምግብ ቤት

አዲስ አበባ ላይ ባለትዳርና ሁሉ ነገር የሞላላት ብትሆንም መሥራት ግን ትፈልጋለች። ለዚህም ሥራ መምረጥን አትሻም። በቀላሉ እከውነዋለሁ ብላ ያሰበችውን የምግብ ሥራ በቤቷ አስቤዛ ከሠራተኛዋ ጋር በመሆን ጀመረች። የሥራ ቦታዋ ምቹ ካለመሆኑም በላይ ለሥራዋ ከባለቤቷም ፍቃድ አላገኘችም ነበር። ግን ቁጭ ብላ መብላትን አትፈልግምና እንደምንም አሳምናው ደንበኞችን አገኝበታለሁ ባለችበት ላምበረት አካባቢ ሥራውን ጀመረች።

በቀን ሥራ የሚተዳደሩና ሊስትሮዎች ይመገቡልኛል የሚል ግምት ነበራትና ፈጣን ምግቦችን ማዘጋጀት ያዘች። በመጀመሪያው ቀን ግን ያሰበችው ቀርቶ ያላሰበችው ሆነ። አንድ መኪና ጎማው ይበላሽና ሁሉም ተሳፋሪ ቤቷን አጥለቀለቀው። ሁለት ሆነው ያን ሁሉ እንግዳ ማስተናገድ ተሳናቸው። ምንም አልተዘጋጁምና ሜኑ አልነበረም። ስንት እንደሚከፈል አልተወሰነም። የሰጧትን እየተቀበለች ሁሉን አስተናግዳ ጠበል ጻዲቅ በሚመስል መልኩ ሸኘች። በዕለቱ ብዙዎቹ እንዳልከፈሏት ታስታውሳለች።

በዚህ ሁኔታም ከሦስት ወር በላይ ቆየች። ሠርታ መመለሷን እንጂ ትርፍና ኪሳራ አለየችም ነበር። ጥፍጥ ያለ ምግብ አዘጋጅታ በትንሽ ዋጋ ትሸጥና ደስተኛ ሆና ወደቤቷ ትመለሳለች። እንዲህ መሆኑ ደግሞ የቤት ኪራይ ጭምር ከባሏ እንድትጠይቅ አስገደዳት። ሁኔታው ግን ከጊዜ ወደጊዜ ያሳስባት ገባ። ስጋት ያዛት። ነገሮችን መቀየር እንዳለባት በማሰብ ለቤቱ ባይመጥንም የወጥቤት ሠራተኛ ቀጠረች። ምግቡን በሚመጥን ዋጋ ማቅረብ የጀመረችው ከዚህ ጊዜ በኋላ ነበር።

ዋጋው የተመጣጠነ በመሆኑ ከሩቅ ጭምር እየመጡ የሚመገቡ ደንበኞችን አፈራች። ይህ ደግሞ ሥራዋን በትልቁ እንድታስበው አደረጋት። በተለይ የላምበረት መናኸሪያ ሲከፈት ብዙ ደንበኞች ወደእርሷ እንደሚተሙ ገመተች። በሠራተኛም ሆነ በቦታው ሰፋ ብላ መሥራት እንዳለባት አወቀች።

መገናኛ አካባቢ ቋሚ ስፍራዋን አድርጋ የምግቡን ሥራ ማጧጧፍ ቀጠለች። ደንበኞቿ በመብዛታቸው ቦታው ሊችላቸው አልቻለም። በዚያ ላይ ፎቁ ላይ ተመሳሳይ ሥራ የሚሠሩ ስለነበሩ ቅሬታ ያቀርቡባት ጀመርና አከራዮቿ አስለቀቋት። እናም ለወራት ሥራዋን አቁማ ቆየች። ተስፋ መቁረጥ ባህሪዋ አይደለምና ዳግመኛ ከቦታው ሳትርቅ ቤት ፈልጋ ሥራውን ጀመረች።

በአዲስ መልኩ የተከራየችው ቤት ብዙዎች የከሠሩበትና ውድ ዋጋ የወጣለት ነው። በቂ ገንዘብ በእጇ ላይ ሳይኖር ለመከራየት ወሰነች። መለኛነቷን ተጠቅማ እቁብ ቀድማ ወሰደች። ቤተሰቤ ከምትለው አንድሰው ገንዘብ ተበድራም የልቧን አደረሰች። ቤቱን በከፈተች በሳምንቱም እቁቧን መክፈል እንደጀመረች አትረሳም። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በአካባቢው ላይ በስፋት መታወቋ ነበር። እናም ዳግመኛ ደንበኞችን ለማምጣት ሳትቸገርና ሳትከስር ሌላ አማራጭ ሰጥቷት ዛሬ ድረስ ቀጥላለች።

## ጠላን በመሀል ከተማ

ከምግቡ ጎን ለጎን በትንሹ ጠላ እየጠመቀች ለደንበኞቿ ትጋብዛለች። ይህ ደግሞ ወደቢዝነስ እንድትቀይረው ይገፋፋት ጀመር። እናም ጎን ለጎን መሥራቱን ያዘች። ከተጠቃሚ ብዛት አንጻር ግን በቦታው መቀጠል አልቻለችም። ምክንያቱም የጠላ ቤት ጨዋታ በቀላሉ የሚገታ አይደለም፤ ሙዚቃና ጭፈራውም እንዲሁ። አሁንም አዲሶቹ አከራዮቿ ይህንን ሊወዱላት አልቻሉም። ቦታውም ቢሆን ጠቧታል። በዚህም ጉዳዩን አስረድታ የሚያከራያትን ሰው ፈለገች።

ዛሬን አመስግና ከማትጠግበው የዋች ሕንፃ ባለቤት ጋር ተገናኘች። ይህኛው አከራይ ባህሉን የሚወድ እንደሆነ በአደረገላት ነገር ያስታውቃል። መጀመሪያ ጠላው እስኪለመድ በሚል የቤት ኪራይ አልተቀበላትም። ሲለመድ ደግሞ በቅናሽ ዋጋ ኪራዩን ተቀበላት። ዝናሽ ይህንን ማበረታቻ ስታይ በተለምዶ ቁመታቸው ዝቅ ባሉ መደቦች ላይ የሚዘወተረውን ጠላ ለዘመናዊ መጠጦች የተዘጋጁ በሚመስሉ መቀመጫዎች ከፍ አድርጋ መሥራቷን ቀጠለች።

እንደተለመደው ጣሳ ሳትሰቅልና ማስታወቂያ ሳትለጥፍም አራተኛ ፎቅ ላይ እንድታስተናግድም ሆነች። ባለሙያዋ ጠጪዎቿን ሳይቀር ቀይራለች። ቦታው የተማረና ባህሉን የሚወድ ጨዋ ሰው የሚታደምበት በመሆኑ ደንበኞቿ ደስተኞች ናቸው። ጠላን በዚህ መልኩ ማግኘት በመቻላቸው እጅጉን ወደውታል።

«ደሸሾ» በሚል ስያሜ የተሰጠው ምግብ ቤትና ባህላዊ መጠጥ ቤቱ ከ50 በላይ ሠራተኞችን በቋሚነት ቀጥሯል። ባህላዊ መጠጦቹ ጠላ፤ ጠጅና አረቄ ከምግብ ጋር አብረው ይቀርባሉ። ጎን ለጎንም የጽሕፈት መሣሪያዎች መደብር (ስቴሽነሪ) በመክፈት ቋሚ ሠራተኞችን ቀጥራ ታሠራለች። በተለይም የፈጠረችው የሥራ ዕድል የቀን ሠራተኞችን ሲጨምር ከመቶ ሰው በላይ ነው። ይህ ደግሞ በትንሽ ገንዘብ ተነስታ ለብዙዎች ተስፋ የሆነች ሴት ያደርጋታል።

ዝናሽ ጠላ ቂጣውን፣ ብቅሉን፣ አሻሮና ሌሎች ነገሮችን ነጣጥላ በመሥጠት ቋሚ ሠራተኞቹን ታሠራቸዋለች። ሁኔታዎች የሚከብዷቸው መስሎ ከተሰማት ደግሞ የጉልበት ሠራተኛን ትጨምርላቸዋለች። በዚያ ላይ ቀን በቀን የጉልበት ሠራተኛው እህልና መሰል የወፍጮቤት ሥራዎችን እንዲከውኑ ታደርጋለች። ይህ ደግሞ በጊዜና በጥራት ባህላዊ መጠጦቹ እንዲዘጋጁ ያግዛታል።

በእነ ዝናሽ ጠላ ቤት የውጭ መስተንግዶ «ቴክ አዌ» የሚባል አሠራር አለ። ለነብሰጡሮች፤ ብቻቸውን መጠጣት ለማይወዱ ሰዎች ቤታቸው ወስደው እንዲጠጡ ዕድሉ ይሰጣቸዋል።

መጀመሪያ አካባቢ ሥራው እስኪለመድና የሚመጣው ሰው በቅጡ እስኪታወቅ ማንኛውም ባህላዊ መጠጥ በብዛት አይዘጋጅም ነበር። የሰዎች ቁጥር ሲበራከትና ደንበኞች የፍላጎታቸውን ማግኘት ሳይችሉ ሲቀሩ ግን ሥራውን አስተካከለች በዚህም በቂ የሆነ መጠጥ አዘጋጅቶ በማቅረብ የለም የሚል ነገር አጠፋች። አሁን በእነርሱ ቤት በየቀኑ ባህላዊ መጠጦች አሉ። በዚህ ደግሞ እየበሉ፤ እየጠጡ ባህላዊ ሙዚቃን እየኮመኮሙ በቤቱ ውስጥ የሚዝናኑ ሰዎችም ቁጥር ተበራክቷል።

## ምክር

ችግር የሌለው ሥራ የለምና ሁሉንም በትዕግስት ማሳለፍ ይገባል፤ እኔ በሥራዬ ትልቅ ችግር ሆኖብኝ የነበረው አተላ መድፊያ ነው። ከመጸዳጃ ሲጨምሩት ፍሳሽ አስወጋጆቹ ባዕድ ነገርን አንመጥም በማለት ያስቸግራሉ። አሁን ላይ «እፎይ» ያልኩት አተላውን ጭኖ ወደሱሉልታ የሚወስድ ሰው በማግኘታቸው ነው ትላለች።

ዝናሽ ጠላን ወደ ውጭ የመላክ ህልም አላት። ምርቱ አገርን በተለያየ መልኩ ያሳድጋል። የመጀመሪያው ባህልን ማስተዋወቅ ሲሆን ሌላው የእርስ በእርስ ትስስርን ማጠናከር ነው። ከዚህ በተጨማሪም ወደ ውጭ በመላክ ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ምንጭም ይሆናል። ሁሉም ባለበት የሚያበረክተው ቁም ነገር አለውና መልካሙን ሁሉ ያድርግ ትላለች።

ዝናሽ «ባህላችንን ማሳደግ ከፈለግን ማንነታችንን አንርሳ፤ ባህል ማለት ዘመኑን የሚዋጅና ከዘመኑ ጋር የሚራመድ ነው፤ ወደ ኋላ የሚጎትተንን፤ ማንነታችንን የሚያጠለሽብንን ነገር ወደጎን እየተውን የሚያበረታንን ነገር እየያዝን ወደፊት መጓዝ አለብን» ትላለች።

«ሴቶች በብዙ ትግል ውስጥ እያለፉ መልካሙን ወይን እያጠጡ ሲያስጉዟችሁ ጫናዎችን አታሳርፉባቸው» ለወንዶች ያስተላለፈችው ምክር ነው። በዚህ ውስጥ አልፈው ብዙዎችን ለወግ ማዕረግ ያበቁትን እያሰባችሁ ደግፏቸውም ምክሯ ነው።

ሌላው ማንኛውም ሥራ ልፋት፣ መሰናክል አለው። «አልችልም» ካልን ግን አንራመድበትም። ጥገኛ ሆነን ዓመታትን እንድናሳልፍ እንሆናለን። እናም «እኛ ሴቶች ብልሃታችን ከሌላው የተለየ ነውና ሁሉንም በመቻል ስኬትን እስክንጎናጸፍ ድረስ መልፋት ይኖርብናል።

በሥራው ላይ የተሰማራችሁ ሴቶች ዝቅ ያልኩ ነኝ ብላችሁ ራሳችሁን ማሳመን የለባችሁም። ከፍ የሚባለው ከዝቅታ በመነሳት እንደሆነ እመኑ። እኔ ከምንም ተነስቼ ባህላዊ መጠጦች የሚቀርቡበትን ጨምሮ ሁለት ቦታ ምግብ ቤት፤ የጽሕፈት መሣሪያ መሸጫ(ስቴሽነሪ) ከፍቻለሁ። እናም ተስፋችሁን ባላችሁበት ቦታ ላይ ሁሉ አለምልማችሁ ስኬታማ ለመሆን ሥሩ» የዝናሽ የማሳረጊያ።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

ሰሞኑን በተለያዩ የኢትዮጵያ እንዲሁም የውጭ አገር ከተሞች ጭምር መንግሥትን በመደገፍ፣ አሸባሪውን ቡድን ሕወሓትንና ምዕራባውያንን በመቃወም ሰላማዊ ሰልፎች ተካሂደዋል። እነዚህ ሰልፎች ከ45 ዓመት በፊት በድሬዳዋ የተካሄደን ሰልፍ አስታውሰውናል። በዚህም ለዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን ጋዜጣው ያቀረበውን የዚህን ሰልፍ ዘገባ ልናስታውስ ወደናል። በተጨማሪም የመረ ጥናቸው ዘገባዎች ከ55 ዓመት በፊት የወጡ ሲሆን አንዳንዶቹ የሚያሳዝኑ ሌሎቹም ግርምትን የሚፈጥሩ ናቸው።

**በድሬዳዋ ከተማ ሰላማዊ ሰልፍ ተካሔደ**

ድሬዳዋ(ኢ.ዜ.አ.)፡- በምሥራቅ ጦር ግንባር የዘመተው መደበኛው መለዮ ለባሽ፣ ሚሊሺያው ሠራዊትና አባላት ጦረኛው የአድኃሪው የሶማሌ ገዥ መደቦች ወራሪ ወታደሮች በማንበርከክና ቅስም በመስበር ፍጹም ስትራቴጂካዊ የሆነውን የካራማራ ኮረብታና የጅጅጋን ከተማ በማስለቀቁ የተሰማውን ደስታ በመግለጽ የድሬዳዋ ከተማና የአካባቢው ሕዝብ ከትናንት በስቲያ ከፍተኛ ሰላማዊ ሰልፍ አድርጓል።

በከተማው ውስጥ በሚገኘው የኮካኮላ ፋብሪካ አጠገብ በሚገኘው አደባባይ ላይ በተደረገው በዚሁ የደስታ መግለጫ ሰልፍ ላይ የ፳፫ ቀበሌ የሴቶችና የወጣቶች የገበሬዎች ማህበራት አባሎች የመንግሥት ሠራተኞች የማምረቻና ሰበነክ ወዛደሮች የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽህፈት ቤት አንቂ ጓዶችና ወታደራዊ ካድሬዎች የፖሊስ አባሎች መምህራን ተማሪዎች በጠቅላላው ቁጥሩ ከ፺፫ ሺ የማያንስ ሕዝብ ተካፋይ ሆኗል።

ከጦር ሜዳ ትግሉ ጀርባ በደጀንነት ተሠልፎ ዘማቹ ሠራዊት አብዮታዊውን ጦርነት በአሸናፊነት እንዲወጣ የሞራል የስንቅ እርዳታ የሚያደርገው ይኸው የከተማውና የአካባቢው ሕዝብ በየማኅበሩና በየሙያ አርማ ሥር ተሰልፎ ደስታውን ለመግለጽ ወደ አደባባይ በተጓዘበት ወቅት «አሻግሮ ገዳይ በረሃ ያለውን ጠላቱን ዛሬ አመድ አረገው» በማለት ወኔን የሚቀሰቅሱ መዝሙሮች ሽለላና ፉከራዎች አሰምቷል።

(የካቲት 29 ቀን 1970 የታተመው አዲስ ዘመን )

**ዝንጀሮዎች ሰው ገደሉ**

ጐፋ (ኢ-ወ-ም) በገሙ ጐፋ ጠቅላይ ግዛት በጐፋ አውራጃ በጐፋ ወረዳ ኰስቲ በተባለው ቀበሌ ሺበሺ ሌንሳ የተባለው የ፲፪ ዓመት ዕድሜ ያለው ልጅ የበቆሎ ሰብል ሲጠብቅ ዝንጀሮዎች በቆሎውን ለመብላት መጥተው ሊያባርራቸው ቢሞክር ተሰብስበው በመያዝ እየጐተቱ የገደሉት መሆኑን የአውራጃው ፖሊስ አስተዳደር በጽሑፍ መግለጣቸውን ዋናው ጸሐፊ አቶ ታደሰ ለገሠ አስታወቁ።

( መስከረም 1 ቀን 1960 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን )

**ሰይጣን አርግዣለሁ የሚለው ወህኒ ቤት ገባ**

አመያ (ኢ-ዜ-አ-) ቤኩማ ተረፈ፣ ማሞ ዘለቀ፣ አበበ ገሩና ለገሠ መኩሪያ የተባሉ ሰዎች በጨቦና ጉራጌ አውራጃ አመያ ወረዳ ግዛት ውስጥ ሽባ እየመሰሉ በልመና ተግባር ተሠማርተው በመገኘታቸው በእሥራት እንዲቀጡ ተደርጓል።

ቤኩማ ተረፈና ለገሠ መኩሪያ እያንዳንዳቸው በአራት ወራት እሥራት፣ እንደዚሁም የቀሩት ሁለቱ በሦስት ሦስት እሥራት እንዲቀጡ መደረጉን የወረዳው ፍርድ ቤት ዳኛ አቶ ዓለማየሁ አስረድተዋል። ከነዚህ ውስጥ በተለይ ቤኩማ ተረፈ የተባለው ሰው የሦስት ዓመት ሰይጣን አርግዤ ወደ ሐኪም ቤት የምገባበት እርጠቡኝ እያለ በማታለል ሆዱን በጨርቅ ጠቅልሎ በማሠር እየተንፏቀቀ ይለምን ነበር።

አድራጐቱ እውነት ያልመሰላቸው አቶ አንጋሳ ነገራ የተባሉ ሰው በቤኩማ ሆድ ላይ የታሠረውን ጨርቅ ቢፈቱት ስለተጋለጠ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወስደው ፍርዱን እንዲያገኝ አድርገዋል ሲሉ አቶ ዓለማየሁ አረጋገጡ።

ለገሠ መኩሪያ የተባለውም ሰው እጁን በጨርቅ እየጠመጠመ ሽባ በመምሰል ሲለምን የተገኘ መሆኑን የገለጡት ዳኛ የቀሩት በተመሳሳይ አድራጐት መገኘታቸውን አስረድተዋል።

( መስከረም 22 ቀን 1960 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን )

**መዛኞች ፪ሺ፫፻ ሰዎችን አስቀጡ**

የአውራ ጐዳና ባለሥልጣን የክብደትና ልክ መወሰኛ ክፍል ከነሐሴ እስከ ጳጉሜ ፭ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ፣ በአምስቱ ዋና በሮች ማለት በደሴ ፣ በሞጆ፣ በጐጃም፣ በነቀምቴና በጅማ መስመሮች በሕዝብና በጭነት ተሽከርካሪዎች ላይ ቁጥጥር አድርጓል።

በተደረገውም ቁጥጥር ፮፻፹፭ ባለተሽከርካሪዎች የትራፊክን ሕግ በመተላለፋቸው ተከስሰዋል። ከተከሰሱትም ውስጥ ፩፻፷፫ቱ ፍርድ ቤት ቀርበው ፲፫ ሺህ ፭፻፶፪ ብር ተቀጥተዋል። የቀሩት ፭፻፲፪ ቱ ገና በቀጠሮ ላይ መሆናቸው ተገልጧል።

እንዲሁም ፬፻፲፱ መንገደኞች በቦታ ጥበት ምክንያት በመጉላላታቸው ከላይ የተጠቀሰው ቅጣት በአሽከርካዎች ላይ መወሰኑን ጭምር የባለሥልጣኑ የማስታወቂያ ክፍል አረጋግጦአል።

( መስከረም 12 ቀን 1960 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን )

**የታንዛንያ ጠንቋዮች በረዶ አዝንመው ታሰሩ**

ከዳሬሰላም (ሮይተርስ)፡- በታንዛንያ ውስጥ በኪጐማ ቀበሌ የሚኖሩ ጠንቋዮች የቀበሌውን የአየር ጠባይ እንዲቆጣጠሩ በየዓመቱ ድርጐ ይከፈላቸው ነበር።

ነገር ግን ሕዝቡ ድርጐአቸውን ስላስቀረባቸው በረዶ የተቀላቀለበት ኃይለኛ ዝናም አዝንመው እህል እንዲበላሽ በማድረጋቸው ተወንጅለው ታስረዋል።

በምዕራብ ታንዛንያ በኪጐማ ቀበሌ አቅራቢያ በሚገኝ መንደር ውስጥ የሚኖሩ ገበሬዎች በሚኖሩበት ቀበሌ ላይ የውሃ መጥለቅለቅና ድርቀት ቢደርስ ይድረስ ብለው በመቁረጥ የዓመት ድርጐአቸውን አንከፍልም ብለው ነበር። ይህንንም እንዳሉ ወዲያውኑ የቀበሌውን እህል ሊያጠፋ የቻለ በረዶ ጥሏል። ወደፊትም በቀበሌው ላይ ከፍተኛ በረዶ ለማውረድ ዝተዋል።

( የካቲት 17 ቀን 1960 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን )

# ዓለም አቀፍ



## በፊሊፒንስ ተማሪዎች የጸረ-ኩረጃ ባርኔጣዎች ማድረጋቸው እያነጋገረ ነው

የፊሊፒንስ ተማሪዎች ኩረጃን ለመከላከል በሚል ወደ መፈተኛ ክፍሎቻቸው አድርገዋቸው የገቡት ባርኔጣዎች ወይም ፊት መሸፈኛዎች በመላው ፊሊፒንስ ግርምትን አጭረዋል። ሌጋዝፒ በተሰኘች አንዲት ከተማ በሚገኝ ኮሌጅ ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የጓደኞቻቸውን የፈተና ወረቀት እንዳያዩ የሚጋርድ ባርኔጣ ፈጥረው ይዘው እንዲመጡ ተጠይቀው ነበር።

በዚሁ መሠረት ተማሪዎቹ በየቤታቸው ካሉ ቁሳቁሶች ባርኔጣቸውን አዘጋጅተዋል። አንዳንዶቹ ከእንቁላል መያዣ ሌሎቹ ከካርቶን ኮፊያቸውን አዘጋጅተው በፈተና ክፍል ውስጥ ተገኝተዋል። ተማሪዎቹ ይህንን እንዲያደርጉ ያዘዙት መምህርት «ተማሪዎቼ በሚያዝናናቸው መንገድ ታማኝነትን እንዲያረጋግጡ ስለፈለግኩ ነው ይህንን እንዲያደርጉ የጠየኩት» ሲሉ ለቢቢሲ ተናግረዋል።

በቢኮል ዩኒቨርሲቲ የምህንድስና ኮሌጅ የመካኒካል ምህንድስና ፕሮፌሰር የሆኑት ሜሪ ጆይ ማንዳኔ ሃሳባቸው «በእርግጥ ውጤታማ» ነበር ብለዋል። በጥቅምት ወር ውስጥ በሚደረገው በዚሁ ፈተና በመቶዎች የሚቆጠሩ የኮሌጁ ተማሪዎች ይህንኑ ጸረ ኩረጃ እርምጃ ተግብረዋል።


ፕሮፌሰር ማንዳኔ ከዓመታት በፊት በታይላንድ ተመሳሳይ ርምጃ ተወስዶ መመልከታቸውን እና ይህም ለእርሳቸው ሃሳብ መነሻ እንደሆነ ተናግረዋል። የፊሊፒንሷ ፕሮፌሰር ማንዳኔ ይህንን ሃሳብ ለምህንድስና ተማሪዎቻቸው ካቀረቡ በኋላ ተማሪዎቹ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ በአቅራቢያቸው ከሚያገኟቸው ቁሳቁሶች ሠርተው መምጣታቸውን ተናግረዋል።

እንዲሁም የአንዳንድ ተማሪዎች መሸፈኛ ውስብስብ ፈጠራ የታየበት መሆኑንም ገልጸዋል። ሌሎች ተማሪዎች ደግሞ ግዴታቸውን ለማሟላት በማሰብ መደበኛ ኮፊያዎቻቸውን ጨምሮ እምብዛም ፈጠራ ያልታየባቸውን መሸፈናዎች ይዘው መጥዋል። መምህሯ የተማሪዎቹን ፎቶ የያዘው የፌስቡክ ልጥፋቸው በጥቂት ቀናት ውስጥ ብቻ በርካታ ሺ ሰዎች በማሕበራዊ መገናኛ ዘዴዎች የተቀባበሉት ሲሆን፣ በፊሊፒንስ መገናኛ ብዙኃንም መነጋገሪያ ሆኖ ቆይቷል።

በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎች የጸረ ኩረጃ የፊት መሸፈኛ እንዲያዘጋጁ አነሳስቷቸዋል ተብሏል። ፕሮፌሰሯ እንዳሉት ተማሪዎቻቸው በዚህ ዓመት የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል። ይህም ጠንክረው በማጥናታቸው እና በፈተናዎች ወቅት በተደረጉ ጥብቅ ፍተሻዎች አማካኝነት ነው። መምህሯ በዚህ ዓመት አንድም ተማሪ ለመኮረጅ ሲሞክር አልተያዘም ሲሉ መናገራቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

## ቦሪስ ጆንሰን ከምርጫ ራሳቸውን በማግለላቸው በተፎካካሪያቸው ተሞገሱ

ሪሺ ሱናክ የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰንን በይፋ አሞገሱ። ሙገሳው የመጣው ጆንሰን ለጠቅላይ ሚኒስትርነት በድጋሚ እንደማይወዳደሩ ካስታወቁ በኋላ ነው። «ቦሪስ ጆንሰን ብሬግዚት እና የክትባት ስርጭት ላይ ስኬታማ ነበሩ» ሲሉ ሪሺ ሱናክ በትዊተር ገጻቸው ላይ አስፍረዋል።



ሪሺ ሱናክ

«ፈታኝ ከሆኑ ጊዜያቶች በአንዱ አገራችንን መርተዋል። ፑቲን በዩክሬን የጀመሩት አረመኔያዊ ጦርነት ወቅትም ነበሩ። ለዚህም ሁሌም እናመሰግናቸዋለን።» በቀጣይ የዩናይትድ ኪንግደም ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን የተሻለ ዕድል አላቸው የተባሉት ሪሺ ሱናክ «በድጋሚ ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን ፍላጎት ባይኖረውም በአገር ውስጥ እና በውጭ መንግሥታዊ ኃላፊነቱን እንደሚወጣ አምናለሁ» ብለዋል።

በተሾሙ በ45 ቀናት ስልጣን በቃኝ ያሉትን የዩኬ ጠቅላይ ሚኒስትር ሊዝ ትረስን ለመተካት የሚደረገው ውድድር ቀነ ገደብ ተቃርቧል። ሪሺ ሱናክ የቀድሞ የጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን አጋሮችን ጨምሮ ከፓርቲያቸው 128 የፓርላማ አባላትን ድጋፍ በመሰብሰብ ውድድሩን እየመሩ ይገኛሉ ተብሎ ነበር።

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን በ53 የድምጽ ድጋፍ ሁለተኛ ሆነው እየተከተሉ ስለመሆናቸው ቢቢሲ መረጃ አግኝቷል። ሆኖም ደጋፊዎቻቸው ወደ ውድድሩ ለመግባት የሚያስፈልገው የድምፅ ድጋፍ እንዳላቸው በመጥቀስ 100 የፓርላማ አባላት የድጋፍ ድምጽ እንዳገኙ ይከራከራሉ። ቦሪስ ጆንሰን የሕዝብ እንደራሴዎች ድጋፍ ቢኖረኝም «አሁን ይህንን የማድረጊያው ትክክለኛ ጊዜ አይደለም። በፓርላማ ውስጥ የተዋሃደ ፓርቲ ሳይኖር ማስተዳደር ይከብዳል» ብለዋል።

እስከ 102 የሚደርሱ የሕዝብ እንደራሴዎች ድጋፍ እንዳላቸውም አስታውቀዋል። ቢቢሲ 57 የሕዝብ እንደራሴዎች እንደሚደግፏቸው በይፋ ቢያረጋግጡም የቀሪዎቹን ለማረጋገጥ አልቻለም። ፔኒ ሞርዳውንት ውድድሩን መቀላቀላቸውን በይፋ ያሳወቁ ብቸኛ ዕጩ ናቸው ነገር ግን በ23 የፓርላማ አባላት ድጋፍ ወደ ኋላ ቀርተዋል።

የቢቢሲዋ ላውራ ኩንስበርግ ቦሪስ ጆንሰን እና ሪሺ ሱናክ ቅዳሜ አመሻሹ ላይ ተገናኝተው እንደነበር ገልጻ፣ ነገር ግን በውይይታቸው ላይ መግለጫ ይወጣ እንደሆነ እርግጠኛ አልነበረችም። ቢቢሲ ድጋፍ የሰጡ የፓርላማ አባላትን መረጃ ሲሰበስብ ቆይቷል። ከ357 ወግ አጥባቂ የፓርላማ አባላት መካከል የ204ቱ የመምረጥ ፍላጎታቸው የሚታወቅ እና በቢቢሲ የተረጋገጠ ሲሆን የበርካቶች ፍላጎት ግን እስካሁን ግልጽ አልሆነም።

የፓርቲው የፓርላማ አባላት አንድ ዕጩን ብቻ የሚደግፉ ከሆነ ሰኞ ከሰዓት በኋላ ዩናይትድ ኪንግደም አንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሊኖራት ይችላል። ካልሆነ ግን የወግ አጥባቂ ፓርቲ አባላት ምርጫ በኦንላይን የሚያካሂዱ ሲሆን ውጤቱም በመጪው ሳምንት አርብ ይፋ ይሆናል።

የምርጫ አስተያየቶች እንደሚያሳዩት በዚህ ኦንላይን ምርጫ ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን ከምርጫው ራሳቸውን ባያገሉ ኖሮ የአባላቱን ድምጽ ሊያሸንፉ እንደሚችሉ ተገምቶ እንደነበር የዘገበው ቢቢሲ ነው።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን ማክሰኞ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ዮሚፍ ቀጄልቻ የኢትዮጵያን የግማሽ ማራቶን ክብረወሰን አሻሻለ

ብርሃን ፈይሳ

ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በሳምንቱ መጨረሻ በተለያዩ የጎዳና ላይ ውድድሮች ውጤታማ በመሆን አጠናቀዋል።ከእነዚህ መካከል አንዱ በስፔን ቫሌንሲያ የተካሄደው የግማሽ ማራቶን ውድድር ሲሆን፤ ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም ከተፎካካሪዎቻቸው ጋር ከፍተኛ ትንቅንቅ በማድረግ በውጤታማነት አጠናቀዋል።በመላው ዓለም ከሚካሄዱ የ21ኪሎ ሜትር ሩጫዎች መካከል ከቀዳሚዎቹ አንዱ የሆነው የቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን በበርካታ አትሌቶች ዘንድ ተመራጭ ነው።በተለይ በከተማዋ ባለው ምቹ የአየር ሁኔታ ምክንያት ፈጣን ሰዓት የሚመዘገብበት በመሆኑም ይታወቃል።

ከትናንት በስቲያ በተካሄደው በዚህ ውድድር ግን የተጠበቀው ሳይሆን እጅግ ሞቃታማ በነበረው የአየር ሁኔታ ምክንያት ውድድሩ ፈጣን እንዳልነበረ ታይቷል።እስከ 10ኛው ኪሎ ሜትር ድረስም አስር የሚሆኑ አትሌቶች 27:51 በሆነ ሰዓት የሸፈኑት ሲሆን፤ ከ13ኛው ኪሎ ሜትር አንስቶ ግን ውድድሩ የነበረበት ሁኔታ መለወጡ ታይቷል። የቀድሞ የርቀቱ ክብረወሰን ባለቤት ኬንያዊው ኪብወት ካንዳይ እና የሃገሩ ልጅ ዳንኤል ማቲኮ እንዲሁም ኢትዮጵዊያኑ ዮሚፍ ቀጄልቻና ታደሰ ወርቁ በመሆን የአሸናፊነት ፉክክር ውስጥ ሊገቡ ችለዋል።እስከ 20ኛው ኪሎ ሜትር ድረስም በመካከላቸው የነበረው ርቀት የ23 ሰከንዶች ብቻ ነበር።

ከፍተኛ ፉክክርና የአሸናፊነት ትንቅንቅ በተደረገበት



አትሌት ዮሚፍ ቀጄልቻ የኢትዮጵያ የግማሽ ማራቶን ክብረወሰን ባለቤት ሆኗል፤

በዚህ ውድድር ላይም በርቀቱ ታዋቂ የሆነው ኬንዊው አትሌት ኪብዎት ካንዳይ 58:10 በሆነ ሰዓት አሸናፊነቱን አረጋግጧል።አትሌቱ በርቀቱ ሶስተኛውን ፈጣን ሰዓት ሲያስመዘግብ ከሁለት ዓመት በፊት በቦታው የክብረወሰን ባለቤት ሲሆን ከገባበት በአንድ ደቂቃ የዘገየ ነው።ለአሸናፊነት ብርቱ ፉክክር ሲያደርግ የቆየው ኢትዮጵያዊው አትሌት ዮሚፍ ቀጄልቻ ደግሞ በ23 ሰከንዶች ዘግይቶ ሁለተኛ በመሆን አጠናቀል።የዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ቻምፒዮናየሁለትጊዜቻምፒዮኑ ዮሚፍ እአአ በ2019 በቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን ሲሮጥ የገባበት ሰዓት 59ደቂቃ ከ05 ሰከንድ ነበር።በዚህ ውድድርም ከአንድ ደቂቃ በላይ የሆነ ፈጣን ሰዓት በማስመዝገብም የኢትዮጵያን የርቀቱን ክብረወሰን ሊሰብር ችሏል።

ኬንያዊው ዳንኤል ማቲኮ እናኢትዮጵያዊው አትሌት ታደሰ ወርቁም በተመሳሳይ ጥቂት ሰከንዶችን ብቻ በመዘግየት በ58 ደቂቃ ሶስተኛ እና አራተኛ ሆነው ውድድራቸውን አጠናቀዋል።ባልተጠበቀ ሁኔታ ሲጀመር ተቀዛቅዞ በፈጠነው በዚህ ውድድር ላይም ስድስት አትሌቶች ከአንድ ሰዓት በታች 21 ኪሎ ሜትሩን መሮጣቸው ታውቋል።

በሴቶች በኩልም በተመሳሳይ ኢትዮጵያዊያን እና ኬንያዊያን አትሌቶች አሸናፊ ይሆናሉ በሚል የተገመተ ቢሆንም የበላይነቱ ግን ወደ ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች ያደላ ነበር።በተያዘው ዓመት የኮፐንሃገን ግማሽ ማራቶን ውድድርን ሁለተኛ ሆና ያጠናቀቀችው ኢትዮጵያዊቷ ጽጌ ገብረሰላማ ርቀቱን በመምራት ሰፊ የአሸናፊነት ቅድመ ግምት ብታገኝም በአራት ሰከንዶች ብቻ በመበለጧ ሳይሳካላት ቀርቷል።1:05:41 በሆነ ሰዓት በመግባትም ጀርመናዊቷ አትሌት ኮንስታንዜ ክሎስተርሃፌን የዘንድሮው የቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን ውድድር አሸናፊ ልትሆን ችላለች።

ሩጫውን ስትቆጣጠር የቆየችው ጽጌ 1:05:45 በሆነ ሰዓት በመግባትም የግሏን ፈጣን ሰዓት ማስመዝገብ ችላለች።ከጽጌ ጋር በመሆን ጠንካራ ፉክክር ስታደርግ የቆየችውና አስቀድሞ ታሸናፋለች የሚል ከፍተኛ ግምት የተሰጣት አትሌት ሃዊ ፈይሳ ደግሞ የሀገሯን ልጅ በመከተል ሶስተኛ ደረጃን ልትይዝ ችላለች።በቫሌንሲያ፣ ኮፐንሃገን እና ባህሬን ግማሽ ማራቶኖች በመሮጥ ልምድ ያላት ሃዊ ርቀቱን የሮጠችበት ሰዓት 1:06:00 ሆኖ ተመዝግቧል።

በሌላ በኩል በስሎቬኒያ በተካሄደው የሉቢኒያ ማራቶን ኢትዮጵያዊው አትሌት ገብረጻዲቅ አብረሃ አሸናፊ መሆኑ ታውቋል።አትሌቱ ርቀቱን 2:06:09 በሆነ ሰዓት ሲሮጥ፤ አትሌት አብደላ ጎዳና ደግሞ 2:08:54 በሆነ ሰዓት አራተኛ ሆኖ ገብቷል።በሴቶችም ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ስራነሽ ይርጋ 2:21:08 በሆነ ሰዓት ቀዳሚ ስትሆን፤ ስንታየሁ ለውጠኝ ደግሞ 2:22:36 በሆነ ሰዓት ሁለተኛ ወጥታለች።በጣሊያኗ ቬነስ በተደረገው ማራቶንም አትሌት ታፈሰ ደለለኝ እና ክብሮም ደስታ ሶስተኛ እና አራተኛ ደረጃን ሲይዙ፤ በሴቶች ፋንቱ ዘውዱ እና ጠጅቱ ስዩም አምስተኛ እና ስድስተኛ ሆነው ውድደሩን ፈጽመዋል።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)
ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

# በኤክስፖርት የቡና ግብይት ተጨባጭ ውጤት እያስመዘገበ የመጣ ዩኒየን

በዳኛቸው ቀደማቸው

ዘመናዊ የምርት ግብይት ስርዓት ግንባታ መነሻ የሚሆኑት መንግስት የቀየሳቸው የገጠር ልማት ፖሊሲዎች፣ስትራቴጂዎችና ስልቶች ናቸው።የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የግብርናውን ዘርፍ ወደ ላቀ ደረጃ ከማሸጋገር አንፃር የፖሊሲዎች መተግበር ወሳኝ ሚና አለው።ለዚህም ውጤት ዋና ሞተር የግብርናውን ምርትና ምርታማነት በላቀ ደረጃ ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ግብይቱ በዘመናዊ መንገድ ሲገነባ ነው።ዘመናዊ የምርት ግብይት በአግባቡ የተደራጀ፣ቀልጣፋ፣ፍትሃዊ ፣ ህጋዊ አሰራር የሰፈነበት የግብይት ሂደት ሊኖረው ይገባል።በሂደቱም ገዥና ሻጭ በተቻለ መጠን በቀጥታ የሚገኙበት ዕድል ይፈጥርባቸዋል፡፡

እሴት የማይጨምሩ ደላሎችን ጣልቃገብነት በማስቀረት አምራቾች በቀጥታ ከገዥዎች /ተጠቃሚዎች/ ጋር በማገናኘት የምርታቸው ዋጋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረጉም በተጨማሪ የገበያ መረጃ በቀላሉ እንዲያገኙና ለምርት ጥራት ዋጋ እንዲሰጡ ያስችላል።በግብይት መካከል ጠንካራ ትስስር ይፈጥራሉ።ከዚህ አኳያ በዘመናዊ ግብይት ዋነኛ ተዋናይ የሆኑት ኅብረት ስራ ማህበራት የማይተካ ሚናቸውን እየተወጡ የሚሄዱበትን ዕድል ይፈጥራል፡፡

ኅብረት ስራ ማህበራት ለሀገራችን ብሎም በክልሉ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ውስጥ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ።ከእነዚህም ተቋማት የቡና አምራች ገበሬዎች ኅብረት ስራ ማህበራት በቀዳሚነት ተጠቃሽ ናቸው።በምዕራብ አማራ በሚገኙ አምስት ዞኖች የሚገኙ የቡና ልማትና ግብይት ኅብረት ስራ ማህበራት የግብይት አድማስ ለማስፋት ያላቸውን እውቀት፣ ገንዘብና የሰው ሃይል በማቀናጀት የኅብረት ስራ ማህበራት አባል መስርተዋል።የእነዚህ አባል ማህበራት ቡና አምራች አርሶ አደር አባላት ብዛት ሁለት ሺ 212 ሲሆን አንድ ነጥብ ሶስት



ሚሊዮን ብር ካፒታል ይዘው የአማራ ቡና ገበሬዎች ኅብረት ስራ ማህበራት ዩኒዬን በሚል ስያሜ እየሰሩ ነው፡፡

አርሶ አደሮቹ ለቡና ልማት እየሰጡት ያለው ትኩረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው። ‹‹ከዓለም የሙቀት መጨመርና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ እየተፈጠረ ያለው የአየር ሁኔታ መፈራረቅ ክልሉ ቡና አብቃይ እንዲሆን መልካም አጋጣሚዎችን ፈጥሯል›› በማለት አካባቢው የተፈጠረለትን አቅም ያመላከቱት በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የተካሄዱ ጥናቶች ናቸው። ከአሁን በፊት ቡና በስፋት ይመረትባቸው የነበሩ ወይና ደጋ የአየር ፀባይ የነበራቸው አካባቢዎች ወደ በረሃማነት እየተቀየሩ ነው። በአንፃሩ ደግሞ በቀዝቃዛማ ይታወቁ የነበሩ ቦታዎች ወደ ወይና ደጋማ እየተቀየሩ እንደሆነ ምልክቶች አሉ። ይህን ተከትሎ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ከደጋማ ወደ ወይና ደጋማ እየተቀየሩ ያሉ የአማራ ክልል የምሥራቅ ጎጃም፣ የምዕራብ ጎጃምና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ባሕር ዳር ዙሪያ ወረዳዎች እንዲሁም የአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር በስፋት ወደ ቡና አብቃይነት እየተሸጋገሩ እንደሆነ በተግባር እየታየ ነው። ለቡና ተክል ተስማሚ የአየር ፀባይ ካላቸው የአማራ ክልል አካባቢዎች መካከል የምዕራብ ጎጃም ዞን ጃቢ ጠህናን ወረዳ አንዱ ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የወረዳው አርሶ አደሮች ቡና ከቤት ፍጆታ ባለፈ ለገበያ ማቅረብ ጀምረዋል።አካባቢው የቡና ተክል ለማብቀል ካለው ተስማሚነትና ምርቱ ለአርሶ አደሩ ሊሰጥ ከሚችለው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንጻር ለዘርፉ ትኩረት እየተሰጠው እንደሚገኝ የማህበሩ ሊቀመንበር ተናግረዋል።

የኅብረት ስራ ማኅበሩ አርሶ አደሮች ከዕለታዊ የቤት ፍጆታነት ወጥተው ምርትን ወደ ውጭ ሀገራት መላክ መጀመራቸውም የዘርፉን ኢኮኖሚያዊ ጮራ የሚያሳይ መሆኑ እየተነገረ ነው። ዩኒየኑ ባለፉት ዓመታት ወደ ጣልያን ፣ጀርመን፣ስዊዘርላንድ፣ አሜሪካ እና ጀርመን ልከው የውጭ ገበያ ተሳትፎ ማድረጋቸውን የዩኒየኑ ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ማሬ ጌትነት ጠቁመዋል። ቡናን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ማምረት ብቻ ሳይሆን በማድረቅ ወቅት የሚከሰትን የጥራት መጓደል ለማሻሻል እየሠሩ መሆኑንም ተናግረዋል። አርሶ አደሮችም ይኽን ተገንዝበው በአግባቡ በማምረት ተጠቃሚነታቸውን እንዲያሳድጉ ጥሪ አስተላልፈዋል። የክልሉ ቡና አምራቾች በ23 መሠረታዊ ማኅበራት የተደራጁ እንደሆኑና ከሁለት ሺ 200 በላይ አባል አርሶ አደሮች እንዳሉትም ሥራ አስኪያጇ አስረድተዋል። የአምራቾችን ቁጥር ለማሳደግም የተለያዩ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶች ተግባራዊ በመደረግ ላይ መሆናቸው ተመላክቷል።

ምዕራብ አማራ ለቡና ምርትና ምርታማነት ምቹ የአየር ንብረት አለው።የአርሶ አደሩ ቡና ለማምረት ፍላጎቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል።በአካባቢው የቡና አብቃይ አርሶ አደሮች ቡናን ገበያ የመሸጥ ልምድ እያደገ መጥቷል።ህገ-ወጥ የቡና ንግድ መስፋፋት፣ ለቡና ግዥ የፋይናንስ እጥረት፣የቡና መፈልፈያና ማበጠሪያ ማሽን በዩኒዬኑም ሆነ በአካባቢው ያለመኖር ችግር እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶቸ ናቸው።ዩኒዬኑ ሲመሰረት የመደራደርና የመምራት አቅም ውስንነት፣ የአባላት ምርትን ተረክቦ ተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ጥራትን መሰረት ያደረገ ግብይት ለማድረግ የጥራት መለኪያዎች /መቆጣጠሪያ/ መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ያለመኖርና ሌሎችን ተዛማጅ ችግሮችን በሚፈለገው ደረጃ እድገት እንዲያስመዘግብ ያላስቻሉት ናቸው።

ሆኖም ያሉትን ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም ማነቆዎች ለመፍታት ጥረት በማድረግ፣ በቡና ምርት ላይ እሴት በመጨመር፣ ለውጪ ገበያ በማቅረብ ለቡና አምራቾች ብሎም ለሀገራችን የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በማስገኘት የበኩሉን አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ይገኛል።ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት ከ188 ሺህ ኪሎግራም በላይ ደረቅ የተጣራ ቡና ለውጪና ለሀገር ውስጥ ገበያ በማቅረብ ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጋ ብር አትራፊ ሆኖ ትርፍ ክፍፍል ለአባላቱ በማከፋፈል ተጠቃሚ አድርጓል።ይህን ጅምር ተግባሩን የበለጠ አጠናክሮ ለማስቀጠል ከአጋር አካላትና ከአባላቱ እንዲሁም ከቡና አምራች አርሶአደሮች ጋር ያለውን ትስስር እያጠናከረ ይገኛል፡፡

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ